# የተመረጡ ፍርዶች

(በወንጀል ህግና የማስረጃ ህግ ላይ ያተኮሩ)

የሰ/መ/ቁ 63014

ሚያዚያ 9 ቀን 2004 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

ነጋ ዱፍሣ

**አመልካቾች፡-** 1. አቶ ወርቅነህ ከንባቶ

2. ወ/ሮ አመለወርቅ ዳሌ

**ተጠሪ፡-** የደቡብ ክልል የሥነ ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍርድ**

ጉዳዩ የቀረበው አመልካቾች የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለት ያቀረቡትን አቤቱታ አጣርቶ ለመወሰን ነው፡፡ ክርክሩ በመጀመሪያ የታየው በሀዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት መደበኛ ጉዳይ ችሎት ነው፡፡ የክርክሩ መነሻ ተጠሪ ያቀረበው የወንጀል ክስ ነው፡፡ ተጠሪ አመልካቾች በ1996 ዓ.ም በወጣው የወንጀል ሕግ አንቀፅ 32/1/ለ እና አንቀፅ 33 እና በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 419 ንዑስ አንቀድ 1 የተመለከተውን በመተላለፍ በወንጀል ግብረ-አበርና ልዩ ተካፋይ በመሆን ምንጩ ያልታወቀ ሀብት ይዘው የመገኘት ወንጀል ፈፅመዋል በማለት ክስ አቅርቧል፡፡ ተጠሪ ባቀረበው የወንጀል ክስ ክርክር በሥር አንደኛ ተከሳሽ የሆነው አንደኛ አመልካች የመንግስት ሠራተኛ ሆኖ ከተቀጠረበት ከመስከረም 1984 ዓ.ም ጀምሮ ክስ እስከ ቀረበበት ድረስ የታክስ አስተዳደርና ገቢ ሰብሳቢ ሆኖ የተለያየ የደረጃ እድገት እያገኘ እንደሠራ ገልፆ፣ አንደኛ አመልካች በሕጋዊ መንገድ በመንግስት ስራው የሚያገኘው ጠቅላላ ገቢ ከብር 90,220 /ዘጠና ሺህ ሁለት መቶ ሃያ/ ብር የሚበልጥ አይደለም፡፡ ነገር ግን ተከሳሾች፡-

- ሁለተኛ ተከሳሽ ዳሽን ባንክ በሒሳብ ቁጥር 50165201 ብር 332,363.63 /ሶስት መቶ ሰላሳ ሁለት ሺህ ሶስት መቶ ስልሳ ሶስት ብር ከስልሳ ሶስት ሳንቲም/ተቀምጦ ይገኛል፡፡
- አንደኛ ተከሳሽ በዳሽን ባንክ በሒሳብ ቁጥር 501651238200114004 ብር 1,646,371.24 /አንድ ሚሊዩን ስድስት መቶ አርባ ስድስት ሺህ ሶስት መቶ ሰባ አንድ ብር ከሃያ አራት ሣንቲም/ በስሙ የሚገኝ ሲሆን
- አንደኛ ተከሳሽ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ሂሳብ ቁጥር 24499 ብር 46,802.11 /አርባ ስድስት ስምንት መቶ ሁለት ብር ከአስራ አንድ ሣንቲም/ በስሙ የሚያንቀሳቅሰው ገንዘብ አለው

- ➢ ተከሳሾች በልጃቸው በደስታ ወርቅነህ ስም ብር 55,931.92 /ሃምሳ አምስት ሺህ ዘጠኝ መቶ ሰላሳ አንድ ብር ከዘጠና ሁለት ሣንቲም/ ግመት ያለው የመኖሪያ ቤት አላቸው፡፡ በጠቅላላው ተከሳሾች ብር 2,081,468.90 /ሁለት ሚሊዮን ሰማኒያ አንድ ሺህ አራት መቶ ስልሳ ስምንት ብር ከዘጠና ሣንቲም/ ምንጩ ያልታወቀ ሀብት ያላቸው በመሆኑ የሙስና ወንጀል ፈፅመዋል በማለት ክስ አቅርቧል፡፡ ተጠሪ ክሱን ሊያስረዱ ይችላሉ የሚላቸውን የሰነድ ማስረጃዎች አቅርቧል፡፡ አመልካቾች ክሱ ከደረሳቸውና እንዲረዱት ከተደረገ በኋላ የወንጀሉን ድርጊት አልፈፀምንም ጥፋተኞች አይደለንም በማለት ተከራክረዋል፡፡ አመልካቾች በበኩላቸው በተጠሪ ክስ የተዘረዘረው ገንዘብ ሕጋዊ ምንጭ የሚሏቸውን በመዘርዘር አቅርበዋል፡፡ አመልካቾች
- ➢ በወንዶገነት ወረዳ አባያ ቀበሌ ከ1984 ዓ.ም ከቤተሰብ የተሰጣቸው 2.5 ሄክታር መሬት የላቸው መሆኑንና ጫት የተከሉ በመሆኑ በዓመት ከመቶ ስልሳ ሺህ ብር በላይ እንደሚያገኙ፣
- ➢ በሌላ በኩል 0.25 ሄክታር የሆነ መሬት እንዳላቸውና የሽንኮራ አገዳ በማልማት በዓመት ሃያ አምስት ሺህ ብር በላይ እንደሚያገኙና በዚህ ገቢ ቤቱን እንደገዙት፣
- ➢ በሁለተኛ ተከሳሽ ስም በዳሽን ባንክ የነበረው ገንዘብ፣ ብር 5,000,000፣ የሚሰራ ፕሮጀክት አንደኛ ተከሳሽ ቀርፆ፣ ከባንክ ብድር ሲጠይቅ አንድ ሶስተኛ አሳይ በመባሉ በብድር የተገኘና ከሁለተኛ አመልካች አካውንት ወጥቶ በአንደኛው አመልካች አካውንት እንደገባና በፍርድ ቤት ትዕዛዝ የታገደ መሆኑን፣
- ➢ በአንደኛው አመልካች ስም ከዳሽን ባንክ ከተገኘው ገንዘብ ውስጥ ብር 1,120,500.00 /አንድ ሚሊዮን አንድ መቶ ሃያ ሺህ አምስት መቶ ብር/ የጋራራም ላንች እና የጋልማ ባሕላዊ ሎጅ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ንብረት ነው በማለት የተከራከሩ ሲሆን ማስረጃዎች አቅርበዋል፡፡

የከፍተኛው ፍርድ ቤት የተጠሪንና የአመልካቾችን ክስና ማስረጃ ከመረመረ በኋላ አመልካቾች የተጠሪን ክስና ማስረጃ ያስተባበሉ መሆኑን ገልፆ ከተከሰሱበት ወንጀል በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ ሥርዓት ሕግ 149 ንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት በነፃ አሰናብቷቸዋል፡፡ ተጠሪ ይግባኝ ለደቡብ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ችሎት አቅርቧል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተጨማሪ ማጣሪያ ካደረገና ተጨማሪ ምስክሮች ከሰማ በኋላ የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔን አፅንቷል፡፡ ተጠሪ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የሰበር አቤቱታ አቅርቧል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የግራ ቀኙን ክርክር ከሰማ በኋላ የአመልካቾችን የመከላከያ ማስረጃ ታዓማኒነትና ክብደት የሌለው በመሆኑ የተጠሪን ክስና ማስረጃ ለማስተባበል አይችልም በማለት አንደኛ አመልካች በሶስት ዓመት ፅኑ እስራት እንዲቀጣ ክስ የቀረበበት ንብረት እንዲወረስ፣ ሁለተኛ አመልካች በአንድ ዓመት ፅኑ እስራት እንድትቀጣ፣ ቅጣቱ እንዲገደብና በስሟ ያለና ክስ የቀረበበት ገንዘብ እንዲወረስ ውሳኔ ሰጥቷል፡፡

አመልካቾች ታህሳስ 5 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር ማመልከቻ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት መሠረታዊ የሕግ ስህተት የማረም እንጂ ፍሬ ጉዳይ የማጣራት ስልጣን አልተሰጠውም፡

፡ዐቃቢ ሕግ በክሱ የጠቀሰውን ገንዘብ ከየት እንዳገኘው አስረድተን እያለ ፍርድ ቤቱ የእኛን የመከላከያ ማስረጃ ውድቅ በማድረግ የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ነው፡፡ የእግድ ትዕዛዝ የተሰጠበት ገንዘብም እንዲወረስ መደረጉ ተገቢነት የለውም፡፡ ስለዚህ በሰበር ታይቶ ይሻርልን በማለት አመልክተዋል፡፡ ተጠሪ በበኩሉ መጋቢት 2 ቀን 2003 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት አመልካቾች ያቀረቡትን የፍሬ ጉዳይ ክርክር የመመርመር ሥልጣን የለውም፡፡ ይህ የሚታለፈ ቢሆን አመልካቾች የወንጀል ክስ ከቀረበባቸው በኋላ በተለይም በይግባኝ በሚሰማበት ጊዜ ያመጡት የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት ውድቅ ያደረገው በአግባቡ ነው፡፡ አመልካቾች ወንጀሉን የፈፀሙ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ ስለዚህ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የለበትም በማለት መልስ ሰጥቷል፡፡ አመልካች መጋቢት 30 ቀን 2003 ዓ.ም የተፃፈ የመልስ መልስ አቅርቧል፡፡

ከስር የክርክሩ አመጣጥና በሰበር የቀረበው ክርክር ላይ የተገለፀው ሲሆን እኛም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ ተገቢ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጭብጥ በመያዝ ጉዳዩን መርምረናል፡፡

1. ጉዳዩን እንደመረመርነው የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሰሚ ችሎት በአመልካቾች ላይ የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ የሰጠው አመልካቾች በሥር ፍርድ ቤትና በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ስለገቢ ምንጫቸው ያቀረቧቸው ምስክሮችና ማስረጃዎች ታዓማኒነት የሌላቸውና የተጠሪን ክስና ማስረጃ ለማስተባበል የሚችሉ አይደሉም በማለት ነው፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሰሚ ችሎት ከዚህ መደምደሚያ ላይ የደረሰ ውሳኔና የሰጠው በተጠሪ በኩል የቀረበውን ማስረጃ ይዘት፣ ታዓማኒነትና ክብደት በዝርዝር በመመርመር በመመዘን እንደዚሁም በአመልካች በኩል የቀረበውን የሰውና የጽሁፍ ማስረጃ በዝርዝር በመመርመርና የማስረጃውን ታዓማኒነትና ክብደት በመመዘን ነው፡፡ በሌላ አገላለፅ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሳኔ የሰጠው የስር ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚው ችሎት ፍሬ ጉዳይ በማጣራትና ማስረጃ በመመዘን ሂደት ፈፅመዋል የማለውን ስህተት ለማረም የማስረጃ ምርመራና ምዘና በመፈፀም ነው፡፡

   ይህም ፍሬ ጉዳይ በማጣራትና ማስረጃ በመመዘን ሂደት በክልሉ ፍርድ ቤቶች ወይም ሌላ የዳኝነት ስልጣን የተሰጣቸው አካላት የፈፀሙት ስህተት ቢኖር የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሰሚ ችሎት ፍሬ ጉዳይ አጣርቶና ማስረጃ መርምሮና መዝኖ የማረም ስልጣን አለው ወይስ የለውም? የሚለውን ነጥብ እንድናይ የሚያስገድደን ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግስት አንቀፅ 80 ንዑስ አንቀጽ 3/ለ/ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበትን በክልል ጉዳዮች ላይ የተሰጠ የመጨረሻ ውሳኔ ለማረም በሰበር ችሎት የማየት ስልጣን እንደሚኖረውና ክርክሩ በሕግ እንደሚወሰን ይደነግጋል፡፡ በ1994 ዓ.ም ላይ ተሻሽሎ የወጣው የክልሉ ሕገ-መንግስት አንቀፅ 75 ንዑስ አንቀፅ 2/ሐ/ የክልሉ ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በክልል ጉዳዮች

የተሰጠ የመጨረሻ ውሳኔ ላይ የተፈፀመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የማረም ስልጣን ያለው መሆኑን በግልፅ ይደነግጋል፡፡ የክልሉ ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 43/1994 አንቀፅ 5 ንዑስ አንቀፅ 3 የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት መሠረታዊ የሕግ ስህተት የፈፀመበትን በክልል ጉዳዮች የተሰጠ የመጨረሻ ውሳኔ ላይ የተፈፀመ መሠረታዊ የሕግ ስህተት የማረም ስልጣን ያለው መሆኑን በግልፅ ይደነግጋል፡፡ ከላይ የጠቀስናቸውን የፌዴራል ሕገ-መንግስት፣ የክልሉ ሕገ-መንግስት የክልሉ አዋጅ ቁጥር 43/1994 ድንጋጌዎች ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት ፍሬ ጉዳይ የማጣራት፣ ማስረጃ የመመርመርና የመመዘን ስልጣን የሚሰጡ ሆነው አላገኘናቸውም፡፡ ስለሆነም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የተጠሪንና የአመልካቾችን ማስረጃ በዝርዝር በመመርመርና በመመዘን የተጠሪን ማስረጃ የወንጀል ክሱን የማስረዳት ብቃትና ታማኝነት አለው፡፡ የአመልካቾች ማስረጃ ታማኝነትና ክብደት የሌለው ነው በማለት የደረሰበትን መደምደሚያና፣ የግራ ቀኙን ማስረጃ መርመሮና መዝኖ የደረሰበትን መደምደሚያ መሠረት በማድረግ በአመልካቾች ላይ የሰጠው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ ከላይ የገለፅናቸውን ድንጋጌዎች የሚጥስና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

2. የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት ፍሬጉዳይ የማጣራት፣ ማስረጃ የመመዘንና የመመርመር ስልጣን የለውም ማለት፣ በክልሉ የሚገኙ ፍርድ ቤቶች ወይም የዳኝነት ስልጣን የተሰጣቸው ሌሎች አካላት፣ መሠረታዊ የሆነ የዳኝነት አካሄድ ስርዓት ሳይከተሉ፣ መመስረት የሚጋባቸውን ጭብጥ ሳይመሰርቱና ጭብጥን የማስረዳት ሁኔታ (Burden of proof) ያለበት ተከራካሪ ወገን የማስረዳት ግዴታውን በአግባቡ እንዲወጣ ሳያደርጉና መጣራት የሚገባውን ፍሬ ጉዳይ ሳያጣሩ የሰጡትን ውሳኔ በሰበር ታይቶ የማረምና በክልሉ የሚገኙ ፍርድ ቤቶች ወይም ሌሎች የዳኝነት ስልጣን የተሰጣቸው አካላት፣ ተገቢውን ጭብጥ በመመስረት፣ በሕግ የማስረዳት ግዴታ የለበት አካል ግዴታውን የተወጣ መሆኑን በአግባቡ መመርመርና በመመዘን እንደዚሁም መጣራት የሚገባውን ፍሬ ጉዳይ አጣርተው እንዲወስኑ ትዕዛዝ የመስጠትና ጉዳዩን የመመለስ የዳኝነት ስልጣን የለውም ማለት እንዳልሆነ ትክክለኛ ግንዛቤ ሊያዝበት የሚገባ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

   በያዝነው ጉዳይ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት በዝርዝር የግራ ቀኙን ማስረጃ በመመዘንና በመመርመር ውሳኔ መስጠቱ መሠረታዊ የሕግ ህተት ያለበት ቢሆንም በውሳኔው የወንጀል ሕግ አንቀፅ 419 በተከራካሪ ወገኖች ከሚጥለው የማስረዳት ግዴታ (Burden of proof) አንፃር አመልካቾችና ተጠሪ በሕግ የተጣለባቸውን ግዴታ ተወጠተዋል ወይስ አልተወጡም? የስር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚ ችሎት በአመልካቾችና በተጠሪዎች መካከል ያለውን አከራካሪ የፍሬ ጉዳይ ጭብጥ ለመወሰን መጣራት የሚገባቸውን ፍሬ ጉዳዮች በማጣራትና የግራ ቀኙን ማስረጃ የሕጉ ድንጋጌ የሚጥልባቸውን የማስረዳት ግዴታ መሠረት በማድረግ በመመርመርና በመመዘን ውሳኔ ሰጥተዋል ወይስ አልሰጡም? የሚሉትን ጭብጦች በውስጡ የያዘ መሆኑን የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት ከሰጠው ውሳኔ ተረድተናል፡፡

ከላይ የገለፅናቸውን ጭብጦች የስር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚ ችሎት በአግባቡ በማየት ውሳኔ የሰጡባቸው መሆን ያለመሆኑን ለመወሰን በመጀመሪያ አመልካቾች የተከሰሱበት የወንጀል ሕጉ አንቀፅ 33 እና 419 ንዑስ አንቀፅ 1 ተጠሪና አመልካች ያለባቸውን የማስረዳት ግዴታ (Burden of proof) መመርመር አስፈላጊ ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ አመልካቾች የተከሰሱበትን የወንጀል ሕግ አንቀፅ 33 እና አንቀፅ 419 ንዕስ አንቀፅ 1 ዝርዝር ይዘት ተመልክተናል፡፡ "ምንጩ ያልታወቀ ንብረትና ገንዘብ" የሚለው ርዕስ ያለው የወንጀል ሕጉ አንቀፅ 419 በንዑስ አንቀፅ 1 "የመንግስት ሠራተኛ የሆነ ወይም የነበረ ማንም ሰው

ሀ/ የኑሮ ደረጃው አሁን ባለበት ወይም አስቀድሞ በነበረበት የመንግስት ስራ ወይም በሌላ መንገድ ከሚያገኘው ወይም ሲያገኝ ከነበረው ሕጋዊ ገቢ የበለጠ እንደሆነ ወይም፣

ለ/ ያለው ንብረት ወይም የገንዘብ ምንጭ አሁን ባለበት ወይም አስቀድሞ በነበረበት የመንግስት ስራ ወይም በሌላ መንገድ ከሚያገኘው ወይም ሲያገኝ ከነበረው ሕጋዊ ገቢ ጋር የማይመጣጠን እንደሆነ፣

የዚህ አይነቱ የኑሮ ደረጃ እንዴት ሊኖረው እንደቻለ ወይም ያለው ንብረት ወይም የገንዘብ ምንጭ በእጁ እንዴት ሊገባ እንደቻለ ለፍርድ ቤት ካላስረዳ በስተቀር እንደሁኔታው የንብረቱ መወረስ ወይም ለባለቤቱ መመለስ እንደተጠበቀ ሆኖ በቀላል እስራት ወይም በመቀጮ ነገሩ ከባድ ሲሆን ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ፅኑ እስራትና በመቀጮ ይቀጣል" የሚል ይዘት ያለው ነው፡፡

ተጠሪ አንደኛ አመልካች ከ1984 ዓ.ም ጀምሮ በዚህ ጉዳይ በወንጀል ክስ አስከቀረበበት ጊዜ ድረስ በክልሉ በተለያየ ደረጃ የመንግስት ሠራተኛ ሆኖ እየሰራ ያገኘው የተጣራና የታወቀ ገቢ ብር 90,220 /ዘጠና ሽህ ሁለት መቶ ሃያ/ ብር መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ እንዳለው በክሱ ከገለፀ በኋላ አመልካቾች በስማቸው በተለየዩ ባንኮች ባላቸው ሂሳብና በልጃቸው ስም የገዙት ቤት ብር 2,018,468.90 /ሁለት ሚሊዩን ሰማኒያ አንድ ሺህ አራት መቶ ስልሳ ስምንት ብር ከዘጠና ሣንቲም/ ያላቸው በመሆኑ ምንጩ ያልታወቀ ሀብት ይዘው ተገኝተዋል በማለት ክስ ያቀረበ ሲሆን ተጠሪ አንደኛ አመልካች የመንግስት ሠራተኛ በነበረበት ጊዜ ያገኝ የነበረውን ገቢ፣ ሁለተኛ አመልካች የቤት እመቤት መሆናቸውንና ንብረቱ በጥሬ ገንዘብ ያለ በስማቸው ያለመሆኑንና አመልካቾች በልጃቸው ስም ቤት ያላቸው መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ እንዳቀረበ ፍሬ ጉዳይ የማጣራትና ማስረጃ የመመዘን ስልጣን ባላቸው ፍርድ ቤቶች ተረጋግጧል፡፡ አመልካቾች በበኩላቸው በባንክ ሂሳባቸው ውስጥ የተገኘው ገንዘብና ቤቱን የሰሩበትን ሀብት ምንጭ ለማስረዳት የመከላከያ ማስረጃዎች እንዳቀረቡ ከስር ፍርድ ቤትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎትና የሰበር ችሎት ከሰጡት ውሳኔ ተረድተናል፡፡

እዚህ ላይ የሚነሳው ጥያቄ አመልካቾች ተጠሪ ያቀረበውንና በማስረጃ ያረጋገጠውን ፍሬ ጉዳይ ማለትም በግልፅ ከሚታወቀውና አንደኛ አመልካች ከ1984 ዓ.ም በመንግስት ሠራተኛነት ያገኝ ከነበረው ሕጋዊ ገቢ በላይ በባንክ ሂሳብ ቁጥራቸው የተገኘው ጥሬ ገንዘብና በልጃቸው ስም ቤት

የሠሩበት ሀብት ማለት ብር 2,081,468.90 /ሁለት ሚሊዮን ሰማኒያ አንድ ሺህ አራት መቶ ስልሳ ስምንት ብር ከዘጠና ሳንቲም/ ትክክለኛ ምንጭ የማስረዳት ግዴታና ኃላፊነት አለባቸው ወይስ የዐቃቢ ሕግን ክስና ማስረጃ ሊያስተባብሉ የሚችሉ አንድ አንድ ፍሬ ጉዳዮችን ለፍርድ ቤት ማቅረባቸው በቂ ይሆናል ወይስ አይሆንም የሚለውን ነጥብ በወንጀል ሕግ አንቀፅ 419 ንዑስ አንቀፅ 1 ድንጋጌ ከተደነገገው የማስረዳት ግዴታ አንፃር መመርመር አስፈላጊ ነው፡፡

ከወንጀል ሕግ አንቀፅ 419 ንዑስ አንቀፅ 1/ሀ/ እና /ለ/ ድንጋጌዎች ለመረዳት የሚቻለው ዐቃቢ ሕግ የመንግስት ሠራተኛ የሆነው ወይም የነበረው ሰው ያገኝ የነበረውና የሚያገኘው ገቢ ምን ያህል እንደሆነና የመንግስት ሠራተኛው በራሱ ስምም ሆነ በቤተሰቡ ስም ከሕጋዊ ገቢው ውጭ ይዞት የሚገኘውን የገንዘብና የንብረት ግምት የማስረዳት ግዴታ ያለበት መሆኑን በግልፅ ተደንግጓል፡፡ በሌላ በኩል የመንግስት ሠራተኛ የነበረው ሰውና ከእሱ ጋር በልዩ አባሪነት የተከሰሰ ሰው የመንግስት ሰራተኛው ሲያገኝ ከነበረውና ከሚያገኘው ገቢ በላይ ይዞ የተገኘው ገንዘብ ወይም ሀብት ትክክለኛው ምንጭ ምን እንደሆነ የማስረዳት ግዴታ እንዳለበት በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 419 ንዑስ አንቀፅ 1 ሶስተኛው ፓራግራፍ፣ "….የዚህ አይነቱ የኑሮ ደረጃ እንዴት ሊኖረው እንደቻለ ወይም ያለው ንብረት ወይም የገንዘብ ምንጭ በእጁ እንዴት እንደገባ ለፍርድ ቤቱ ካላስረዳ በስተቀር" ምንጩ ያልታወቀ ሀብት ይዞ በመገኘቱ /በመገኘታቸው/ ጥፋተኛ ተብለው ዐቃቢ ሕግ በግልፅ ከሚታወቀው ሕጋዊ ገቢ በላይ ነው በማለት በክሱ የገለፀውንና በማስረጃ ያረጋገጠውን ሀብት ትክክለኛ ምንጭ የማስረዳት ግዴታ (Burden of proof) በተከሳሾች ላይ የሚወድቅ መሆኑን ነው፡፡ የተከሳሾች የማስረዳት ግዴታም በዐቃቢ ሕግ በክሱ ከገለፀውና በማስረጃ ካረጋገጠው ውጭ ተከሳሾች ሌላ ገቢ የሚያገኙበት ስራ ወይም የገቢ ምንጭ ያላቸው መሆኑን ብቻ ለፍርድ ቤቱ በማሳየት የሚወሰን ሳይሆን፣ በዐቃቢ ሕግ ክስና ማስረጃ ከተረጋገጠው ገቢ ውጭ በእጅ እንደተገኘ የተረጋገጠው ገንዘብና ሀብት ትክክለኛ ምንጭ ምን እንደሆነ የማስረዳት ግዴታና ኃላፊነት ያለበት መሆኑን ከወንጀል ሕግ አንቀፅ 419 ንዑስ አንቀፅ 1 ሶስተኛው ፖራግራፍ ድንጋጌ አቀራረፅና ይዘት ለመረዳት ይቻላል፡፡

ከዚህ አንፃር ስንመለከተው አንደኛው አመልካች የመንግስት ሠራተኛ ሆኖ ከሚያገኘው ደመወዝ /ሕጋዊ ገቢ/ በላይ በስማቸው በተከፈተ የባንክ ሂሳብና በልጃቸው ስም ቤት የተሰራበትና እንደያዙት የተረጋገጠው በአጠቃላይ መጠኑ ብር 2,081,468.90 /ሁለት ሚሊዮን ሰማኒያ አንድ ሺህ አራት መቶ ስልሳ ስምንት ብር ከዘጠና ሣንቲም/ የሆነ ገንዘብና ሀብት ምንጩ በአንደኛ አመልካች ስም በወንዶገነት ወረዳ አባዮ ቀበሌ ካለው 2.5 ሄክታር መሬት ላይ ካለሙት የጫትና የቡና ሰብል ሽያጭ፣ በሁለተኛ አመልካች ስም 0.25 ሄክታር መሬት ላይ ካለሙት የሰንኮራ አገዳ እንደሆነ፣ ከፊሉን በብድር ከግለሰብ ያገኙት መሆኑንና ከፊሉ የጋራራሙ ላንቶ የእንስሳት ማድለብና ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበርና የጋልማ ባህላዊ ሎጅ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር መሆኑን የሚየሳዩ ማስረጃዎች እንዳቀረቡ ከሥር ፍርድ ቤትና ከይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ውሳኔ ተገንዝበናል፡፡

ሆኖም የስር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት አመልካቾች ያቀረቧቸው ማስረጃዎች አንደኛ አመልካቾች ከሚሰራው የመንግስት ስራ በተጨማሪ ሌላ የገቢ ምንጭ የነበረው መሆኑን የሚያሳዩ ማስረጃዎች መሆናቸውን በመመልከት ብቻ መጣራት የሚገባቸው ፍሬ ጉዳዮችን ሳያጣሩና በተለይም

አመልካቾች በዐቃቢ ሕግ ክስና ማስረጃ ከሕጋዊ ገቢያቸው በላይ የያዙ መሆናቸው ብር 2,081,468.90 ያገኙበትን ትክክለኛ የገቢ ምንጭ የወንጀል ሕጉ አንቀፅ 419 ንዑስ አንቀፅ 1 በሚደነግገው መሠረት የማስረዳት ግዴታቸውን ተወጥተዋል ወይስ አልተወጡም የሚለውን ጭብጥ በመያዝ በሕጉ በአመልካቾች ላይ የተጣለውን የማስረዳት ግዴታ (Burden of proof) መሠረት በማድረግ ተገቢውን ማጣራት አድርገው መርምረውና መዝነው ውሳኔ የሰጡ አለመሆናቸውን ከውሳኔያቸው ይዘት ለመረዳት ችለናል፡፡ ምክንያቱም

ሀ/ አመልካቾች በስማቸው እንዳለና ጫት፣ እንሰት፣ ቡናና ሸንኮራ አገዳ እያለማን ገቢ እናገኝበታለን ያሉት 2.25 ሄክታር መሬት በተመለከተ አመልካቾች የእርሻ መሬቱ ባለይዞታ ናቸው ወይስ አይደሉም? የእርሻ መሬቱ ባለይዞታ ከሆኑ የእርሻ መሬቱን በይዞታነት የያዙት መቼ ነው? መሬቱን በማልማት ኢኮኖማያዊ ጠቀሜታ ያላቸው የተለያዩ ተክሎች በማልማት ምርት ገቢ ማግኘት የጀመሩት መቼ ነው? ከመሬቱ የሚገኘው ገቢና መሬቱን ለማልማትና ምርቱን ለገበያ ለማቅረብ የሚወጣው ወጭ ምን ያህል ነው? አመልካቾች ከመሬቱ ተጣርቶ የሚደርሳቸው ገቢ ምን ያህል ነው የሚለው ፍሬጉዳይ በአግባቡና በገለልተኛ ባለሙያ ተጣርቶ ባልታወቀበት ሁኔታ ከቀበሌና ከዞኑ ግብርና ጽ/ቤት የተፃፉ ደብዳቤዎችን ብቻ መሠረት በማድረግ አመልካቾች ከእርሻ የሚያገኙት ገቢ መጠን ከፍተኛ እንደሆነ መወሰኑ በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 419 ንዑስ አንቀፅ 1 በአመልካቾች ላይ የሚደነግገውን የማስረዳት ግዴታ (Burden of proof) መሠረት በማድረግ ጉዳዩ ተጣርቶ የተወሰነ አለመሆኑን የሚያሳይ በመሆኑ፣

ለ/ አመልካቾች በባንክ ሂሳባቸው ውስጥ ከተገኘው ገንዘብ ውስጥ ብር 1,120,500 /አንድ ሚሊዮን አንድ መቶ ሃያ ሺህ አምስት መቶ ብር/ በአንደኛው አመልካች ስም የተቀመጠ ከፊሉ የጋራራሙ ላንቶ የእንስሳት ማድለብ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ገንዘብ ከፊሉ ደግሞ የጋልማ ባህላዊ ሎጅ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር መሆኑን ለማስረዳት የማህበራቱ ቃለ ጉባኤና አባላት በማስረጃነት ያቀረቡ መሆኑን ከሥር ፍርድ ቤትና ከይግባኝ ሰሚው ችሎት ውሳኔ ተገልጿል፡፡ ሆኖም በመጀመሪያ ደረጃ ኃላፊነታቸው የተወሰኑ የግል ማህበራት የሚመሰረቱት የማህበሩ ዋና ገንዘብ ልክና የማህበሩ ዋና ገንዘብ በሙሉ መግባቱን የሚያስረዳ መግለጫ ሲቀርብ መሆኑ በንግድ ሕጉ አንቀፅ 519 ንዑስ አንቀጽ /መ/ እና /ሰ/ በአስገዳጅነት የተደነገገ በመሆኑ እነዚህ የንግድ ማህበራት ሕጋዊ ሰውነት አግኝተው ተመዝግበው ከሆነ ሲመዘገቡ ያስመዘገቡትና ገቢ ያደረጉት የማህበሩ ዋና ገንዘብ ምን ያህል ነው? ማህበራቱ በካፒታልነት ካስመዘገቡት ካፒታል በላይ በአመልካቾች ስም ለማህበር መመስረቻ የተዋጣው ገንዘብ አለ በማለት የሚጽፉቸው የተለያዩ ማስረጃዎች ሕጋዊ ተቀባይነት፣ ያላቸው ናቸው ወይስ አይደሉም? የሚሉት ነጥቦች ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር አመሰራረት፣ መዋጮ አከፋፈል፣ የማህበሩ ዋና ገንዘብና ገንዘቡ ገቢ ስለሚሆንበት ሁኔታ የተቀመጡ ሕጋዊ መስፈርቶችን በወንጀል ሕጉ አንቀፅ 419 ንዑስ አንቀጽ 1 ያለባቸውን የማስረዳት ኃላፊነት መሠረት በማድረግ ተጣርተው ውሳኔ የተሰጠበት ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ስለሆነም የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚ ችሎት ከላይ የዘረዘርናቸውን መጣራት የሚገባቸውን ፍሬጉዳዮች ሳያጣራና አመልካቾች ያቀረቧቸው ማስረጃዎች በወንጀለ ሕጉ አንቀፅ 419 ንዑስ አንቀፅ 1 የተጣለባቸውን የማስረዳት ግዴታ (Burden of proof) የተወጡ መሆኑን ያለመሆኑን የሚያሳዩና አግባብነት ያላቸውን ሕጎች መሠረት ያደረጉና ተቀባይነት ያላቸው ናቸው ወይስ አይደሉም? የሚለውን ጭብጥ በመመስረት ውሳኔ ያልሰጡበት በመሆኑ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በመሆኑም የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የተጠሪንና የአመልካቾችን ማስረጃ በዝርዝር በመመርመርና በመመዘን የሰጠው ውሳኔም ሆነ የሥር ፍርድ ቤትና ይግባኝ ሰሚው ችሎት ከላይ በዝርዝር የገለፅናቸውን ፍሬጉዳዮችን ሳያጣራና ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸውን የሕግ ድንጋጌዎች መሠረት በማድረግ የአመልካቾችን ማስረጃ ተቀባይነት ሳይመረምሩ የሰጡት ውሳኔ የወንጀል ሕጉን አንቀፅ 419 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌዎችና ከላይ የዘረዘርናቸውን የሕግ ድንጋጌዎች የሚጥሱና መሠረታዊ የሕግ ስህተት ያለባቸው ናቸው በማለት ወስነናል፡፡

**ውሳኔ**

1. የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ችሎት የሰጠው ውሳኔ ተሽሯል፡፡
2. የሀዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት መደበኛ ችሎትና የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሳኔ ተሽሯል፡፡
3. የሀዋሳ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት መደበኛ ችሎት ከዚህ በፊት ጉዳዩን ያላዩት ዳኞች በመሰየም በዚህ ፍርድ በተራ ቁጥር 2/ሀ/ እና /ለ/ የተዘረዘሩትን ነጥቦች በማጣራትና የማስረጃዎቹን ተቀባይነት፣ ክብደትና ተዓማኒነት በመመዘን በወንጀለኛ መቅጫ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ቁጥር 149/1/ መሠረት ፍርድ እንዲሰጥበት ጉዳዩን መልሰንለታል፡፡ የውሳኔው ግልባጭ ይላክለት፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፣ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ ብለናል፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

**በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት**
**የምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍ/ቤት**
**ባሕር ዳር**

**የወንጀል መዝገብ ቁጥር 41634**

ቀን ግንቦት 28/2004 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** 1ኛ. አለኸኝ ብዙአየሁ
2ኛ. ማርቆስ በቀለ
3ኛ. ስሜነህ በላቸው

**ከሳሽ**፡- የአብክመ ሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ዐ/ሕግ ሞገስ ወረታ ቀረቡ
**ተከሳሽ**፡- ዳግም ደሳለኝ ገደቡ ከጠበቃው ከአቶ አደራው ደምለውም ጋር ቀረበ

መዝገቡ ለዛሬ የተቀጠረ ለምርመራ ነው፤ በዚህም መሰረት መዝገቡን መርምረን ቀጥሎ ያለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

**ፍርድ**

የአብክመ ሥነ-ምግባርና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን በቁጥር ፀ/ሙ/40/05/2003 በቀን 14/11/2002 ዓ.ም በተፃፈ የሙስና ወንጀል ክስ ማመልከቻ ተከሳሹ በወንጀል ሕግ አንቀፅ 419(1)(ለ) ስር የተደነገገውን በመተላለፍ ከ1983 ዓ.ም እስከ 30/10/2002 ዓ.ም ድረስ የመንግስት ሰራተኛ ሆኖ ተቀጥሮ ሲሰራ በዚህ ጊዜ ውስጥ የተከፈለው የተጣራ ደመወዝ ድምር ብር 337,978.39 /ሶስት መቶ ሰላሳ ሰባት ሽህ ዘጠኝ መቶ ሰባ ስምንት ብር ከሰላሳ ዘጠኝ ሳንቲም/ ሆኖ እያለ በባሕር ዳር ከተማ ቀበሌ 13 ውስጥ ስፋቱ 206 ካ.ሜ ቦታ ላይ በ163,774.52 ወጭ የተሰራ በስሙ የተመዘገበ አንድ ቪላ የመኖሪያ ቤት፣ በባሕር ዳር ከተማ ቀበሌ 11 ውስጥ ስፋቱ 250 ካ.ሜ ቦታ ላይ የተሰራ በተከሳሹ ባለቤት በወ/ሮ ወለላ አየለ ስም በብር 147,704.14 ከአቶ አበበ አለማየሁ የተገዛ፣ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ባሕር ዳር ቅርንጫፍ በሂሳብ ቁጥር 703501015628 በስሙ የተቀመጠ ብር 101,857.54፣ በዳሽን ባንክ ባሕር ዳር ቅርንጫፍ በቁጠባ ሂሳብ ቁጥር 5020004680008 በስሙ የተቀመጠ ብር 202108.41 እና በዳሽን ባንክ ባህር ዳር ቅርንጫፍ በቁጠባ ሂሳብ ቁጥር 5020519090001 በተከሳሽ ባለቤት በወ/ሮ ወለላ አየለ ስም የተቀመጠ ብር 105,746.74 የተገኘ በመሆኑ ይህ ያለው ንብረትና ገንዘብ አሁን ባለበት ወይም አስቀድሞ በነበረበት የመንግስት ስራ ወይም በሌላ መንገድ ሲያገኘው ከነበረው ሕጋዊ ገቢ ጋር የማይመጣጠን በመሆኑ ምንጩ ያልታወቀ ንብረትና ገንዘብ ማፍራት ወንጀል ፈፅሟል በማለት ክስ የመሰረተ ሲሆን ይህንም ክስ ያስረዳልኛል በማለት 26 ገጽ ያላቸው 11 የሰነድ ማስረጃዎች አያይዞ አቅርቧል፡፡

ተከሳሹም በክሱ መሰረት ፍ/ቤት እንዲቀርብ ተደርጎ የዕምነት ክህደት ቃሉን ሲጠየቅ የተከሰስኩበትን የወንጀል ድርጊት አልፈፀምኩም፤ ጥፋተኛም አይደለሁም በማለት ክዶ ተከራክሯል፡፡ በዚህም ምክንያት ዐ/ህግ ተከሳሹ የተከሰሰበትን የወንጀል ድርጊት የካደ ስለሆነ ከክሳችን ጋር አያይዘን

ያቀረብናቸው የሰነድ ማስረጃዎች ተመርምረው ብይን ይሰጥልን በማለት ስላሳሰቡ የዐ/ህግ የሰነድ ማስረጃዎች እንዲመረመሩ ተደርገዋል፡፡

በዐ/ህግ የሰነድ ማስረጃ ዝርዝር መግለጫ በተራ ቁጥር 9 እና 10 የተጠቀሱት ማስረጃዎች ተከሳሹ በመንግስት ሰራተኝነት ከተቀጠረበት ከመስከረም 03 ቀን 1983 ዓ.ም እስከ ሰኔ 30 ቀን 2002 ዓ.ም ድረስ ያገኘ የነበረውን ደመወዝ የሚገልፅ ሲሆን እሱም ተከሳሹ መጀመሪያ ሲቀጠር በብር 500.00 /አምስት መቶ ብር/ የተቀጠረ መሆኑንና በየጊዜው እድገትና የደመወዝ መሻሻል እየተደረገለት ይህ ማስረጃ እስከተፃፈበት እስከ ሀምሌ 01 ቀን 2002 ዓ.ም ድረስ ብር 3,752.00 /ሶስት ሽህ ሰባት መቶ ሃምሳ ሁለት ብር/ ያገኝ እንደነበረና ከተቀጠረበት ቀን ጀምሮ ይህ ማስረጃ እስከተፃፈበት ቀን ድረስ ያገኘው የተጣራ ደመወዙ ድምር ብር 337,978.14 /ሶስት መቶ ሰላሳ ሰባት ሽህ ዘጠኝ መቶ ሰባ ስምንት ብር ከአስራ አራት ሳንቲም/ እንደሆነ ያስረዳል፡፡

ከተራ ቁጥር 4-7 እና 11 የተጠቀሱት የሰነድ ማስረጃዎች ደግሞ ተከሳሹ በፓሊ ፔዳ ቁጥር 1 የቤት ስራ ማህበር አባል በመሆን ግምቱ ብር 163,774.52 /አንድ መቶ ስድሳ ሶስት ሽህ ሰባት መቶ ሰባ አራት ብር ከአምሳ ሁለት ሳንቲም) የሆነ የመኖሪያ ቤት የሰራ መሆኑን ያስረዳል፡፡

በተራ ቁጥር 8 የተጠቀሰው የሰነድ ማስረጃ ደግሞ ተከሳሹ በባለቤቱ በወ/ሮ ወለላ አየለ ስም በባሕር ዳር ቀበሌ 11 ውስጥ ስፋቱ 250 ካ.ሜ በሆነ ቦታ ላይ የተሰራ አንድ መኖሪያ ቤት በብር 147,704.14 /አንድ መቶ አርባ ሰባት ሽህ ሰባት መቶ አራት ብር ከአስራ አራት ሳንቲም/ የገዛ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

ከተራ ቁጥር 1-3 የተጠቀሱት የሰነድ ማስረጃዎች ደግሞ ተከሳሹ በራሱና በባለቤቱ ስም በባሕር ዳር ንግድ ባንክ እና ዳሽን ባንክ ቅርንጫፎች በድምሩብር 409,712.69 /አራት መቶ ዘጠኝ ሽህ ሰባት መቶ አስራ ሁለት ብር ከስልሳ ዘጠኝ ሳንቲም/ አስቀምጦ የተገኘ መሆኑን ያስረዳሉ፡፡

ፍ/ቤቱም ዐ/ህግ በተከሳሹ ላይ ያቀረባቸውን የሰነድ ማስረጃዎች ሲመረምራቸው ተከሳሹ ከመስከረም 03 ቀን 1983 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ሰኔ 30 ቀን 2002 ዓ.ም ድረስ በሰራባቸው ወደ 20 ዓመታት የሚጠጋ ጊዜ በመንግስት ሰራተኛነት ተቀጥሮ ሲሰራ የተከፈለው አጠቃላይ የተጣራ የደመወዝ ድምር 337,978.14 /ሶስት መቶ ሰላሳ ሰባት ሽህ ዘጠኝ መቶ ሰባ ስምንት ብር ከአስራ አራት ሳንቲም/ ሆኖ እያለ ተከሳሹ አንድ ቤት የሰራበት፣ በሚስቱ ስም ቤት የገዛበት እና በራሱና በሚስቱ ስም በተለያዩ ባንኮች ያስቀመጠው ገንዘብ ድምሩ ብር 721,191.35 /ሰባት መቶ ሃያ አንድ ሽህ አንድ መቶ ዘጠና አንድ ብር ከሰላሳ አምስት ሳንቲም/ ነው፡፡ ይህም የሚያሳየው በአጠቃላይ በሀብቱ ድምር እና ከደመወዝ ባገኘው ገንዘብ መካከል የብር 383,213.21 (ሶስት መቶ ሰማኒያ ሶስት ሽህ ሁለት መቶ አስራ ሶስት ብር ከሃያ አንድ ሳንቲም) ልዩነት ያሳያል፤ በዚህም ምክንያት ይህ በልዩነት የሚታየው ገንዘብ ምንጩ ምን እንደሆነ ስላልታወቀ ተከሳሹ ይህን በልዩነት የሚታየውን ገንዘብ ከየት እንዳገኘው እንዲያስረዳ በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 142(1) መሠረት ሊከላከል ይገባል በማለት ብይን ሰጥቷል፡፡

ተከሳሹ በብይኑ መሰረት ገንዘቡን ያገኘሁበትን ምንጭ ያስረዱልኛል በማለት ስምንት የሰነድ ማስረጃዎች አያይዞና የሰባት ምስክሮችን ስም ዘርዝሮ አቅርቧል፡፡ የተከሳሹ የመጀመሪያው የሰነድ ማስረጃ ተከሳሹ በመንግስት ሰራተኝነት ከተቀጠረበት ከመስከረም 03 ቀን 1983 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ሰኔ 30 ቀን 2002 ዓ.ም ድረስ ያገኝ የነበረውን ደመወዝ የሚገለፅ ሲሆን እሱም ተከሳሹ መጀመሪያ ሲቀጠር በብር 500.00 /አምስት መቶ ብር/ የተቀጠረ መሆኑንና በየጊዜው እድገትና የደመዝ መሻሻል እየተደረገለት ይህ ማስረጃ እስከተፃፈበት እስከ ሀምሌ 01 ቀን 2002 ዓ.መ ድረስ ብር 3752.00 /ሶስት ሽህ ሰባት መቶ ሃምሳ ሁለት ብር/ ያገኝ እንደነበረና ከተቀጠረበት ቀን ጀምሮ ይህ ማስረጃ እስከተፃፈበት ቀን ድረስ ያገኘው የተጣራ ደመወዙ ድምር ብር 337,978.14 /ሶስት መቶ ሰላሳ ሰባት ሽህ ዘጠኝ መቶ ሰባ ስምንት ብር ከአስራ አራት ሳንቲም/ እንደሆነ ያስረዳል፡፡

የተከሳሹ ሁለተኛ የሰነድ መከላከያ ማስረጃ ደግሞ ተከሳሹ ከኢፌዴሪ የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ከየካቲት 24 ቀን 2000 ዓ.ም ጀምሮ የሂሳብ አዋቂ ሆኖ ለመስራት የሚያስችለው የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተሰጠው መሆኑን፣ የባሕር ዳር ከተማ አስተዳደር ንግድ ኢን/ኢን/ማስ/ማስ/ጽ/ቤት በብር 25,000.00 /ሃያ አምስት ሽህ ብር/ ካፒታል የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት የሰጠው መሆኑን እና ይህ የንግድ ምዝገባ ፈቃድም በ2001 ዓ.ም የታደሰ መሆኑን ያስረዳል፡፡

ሶስተኛው የተከሳሹ ማስረጃ ደግሞ የተከሳሹ ባለቤት በምግብ ንጽህና አገልግሎት እና በቤት እቃዎች የንግድ ስራ መስክ በብር 5,000.00 /አምስት ሽህ ብር/ ካፒታል መስከረም 28 ቀን 2002 ዓ.ም የንግድ ስራ ፈቃድ የተሰጣት መሆኑንና ከዚያ በኋላ ያልታደሰ መሆኑን ያሳያል፡፡

አራተኛው የመከላከያ ማስረጃ ደግሞ በአሶሳ ከተማ ውስጥ ነዋሪ የሆኑት ወላጅ አባቴ በአወጡት ንግድ ፈቃድ በሚኖሩበት ከተማ በስማቸው ተመዝግቦ በሚገኘው የይዞታ ቦታቸው 5 ልጆቻቸውን የማህበሩ አባል በማድረግ ባቋቋሙት የብሎኬት ማምረቻ ድርጅት  እኔ በማህበር አባልነቴ የገቢ ምንጭ አገኝ የነበረ መሆኑንና በማህበሩ አባላት ስምምነት በተሰጠኝ ኃላፊነት መሰረት ከብሎኬት ማምረቻ ድርጅቱ የሚገኘውን ገንዘብ በስሜ የማስቀምጥ መሆኔን ያስረዳልኛል የሚል ነው፡፡

አምስተኛው የሰነድ ማስረጃ ደግሞ በአወጣሁት የሂሳብ አዋቂነት የንግድ ፈቃድ መሰረት በባሕር ዳር የመጠጥ ውሃና ፍሳሽ አገልግሎት ጽ/ቤት፣ በአማራ መልሶ ማቋቋም ልማት ድርጅት መ/ቤት፣ በእየሩሳሌም ህፃናት ማሳደጊያ ድርጅት እና በአቶ አሊ እንድሪስ የግል ንግድ ድርጅት ሂሳብ በመስራት ገቢ ያገኘሁ መሆኔን ያስረዳልኛል ተብሎ የቀረበ ነው፡፡

ስድስተኛው የመከላከያ ማስረጃ ደግሞ ከ1986 ዓ.ም እስከ መጋቢት 1998 ዓ.ም በአማራው ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት ውስጥ በአካውንታንትነት፣ በፋይናንስ አገልግሎት ኃላፊነትና በሂሳብ አማካሪነት በንፅፅር ከሌሎች መ/ቤቶች በተሻለ ደመወዝ የሰራሁ እንደሆነና የድርጅቱን የበርካታ ዓመታት ሂሳብ በቡድን መሪነት የትርፍ ሰዓት ክፍያ እየተከፈለኝ ስሰራ መቆየቴን እና ከ10 ዓመት ላላነሰ ጊዜ ድርጅቱ በሰጠኝ የመኖሪያ ቤት ስኖር የቤት ኪራይ፣ የውሃ እና የመብራት ክፍያ ሳልከፍል በመቆየቴ የተሻለ ገንዘብ መቆጠቤን ያስረዳልኛል የሚል ነው፡፡

ሰባተኛው የሰነድ ማስረጃ ደግሞ በ1988 ዓ.ም በማህበር ተደራጅቼ የመኖሪያ ቤቴን ስሰራ ለግንባታው አስፈላጊ የሆኑት ነገሮች ዋጋ አሁን ካለው ዋጋ ጋር ሲነፃፀር በጣም አነስተኛና ዝቅተኛ ስለነበር የቤቱ ግምት ቤቱ በተሰራበት ጊዜ በነበረው ዋጋ ተገምቶ መቅረብ ሲገባው በ2002 ዓ.ም ባለው ዋጋ ተገምቶ መቅረቡ አግባብ ባለመሆኑ በ1988 ዓ.ም የነበረውን የገበያ ዋጋ መሰረት በማድረግ ገለልተኛ በሆነ ባለሙያ ተገምቶ ይቅረብልኝ የሚል ሲሆን ይህንን ዋጋም ገምቶ እንዲያቀርብ የታዘዘው የባሕር ዳር ከተማ አስተዳደር አገልግሎት ጽ/ቤት ተከሳሹ ቤቱን ለማሰራት ያስፀደቀው ዲዛይን ዝርዝር ግምት 163,774.52 /አንድ መቶ ስልሳ ሶስት ሽህ ሰባት መቶ ሰባ አራት ብር ከሃምሳ ሁለት ሳንቲም/ እንደሆነ ያስረዳል፡፡

ስምንተኛው የሰነድ ማስረጃ ደግሞ ተከሳሹ የፓሊና ፔዳን ቁጥር 1 የቤት ስራ ማህበር አባል ሆኖ እንደማንኛውም አባል በየጊዜው በማዋጣት ባጠራቀመው ገንዘብ የመኖሪያ ቤቱን የመሰረት ግንባታ የሰራ መሆኑን ያስረዳል፡፡

ከሰነድ ማስረጃዎች በተጨማሪ ተከሳሹ በቴፒ ቡና ተክል ልማት ድርጅት ከ1983-1985 ዓ.ም ድረስ ለሶስት ዓመታት በሂሳብ ሰራተኛነት ተቀጥሬ ስሰራ ከመደበኛ ደመወዜ በተጨማሪ በሂሳብ መዛግብት ስራ የትርፍ ሰዓት ክፍያ ስለማገኝና ድርጅቱ በሰጠኝ የመኖሪያ ቤት ኪራይ ሳልከፍል በነፃ በመኖሬ የተሻለ ገቢ የነበረኝና ገንዘብ ለመቆጠብ ምቹ ሁኔታ የፈጠረልኝ መሆኑን በወቅቱ አብረውኝ ይሰሩ የነበሩት ሰዎች ያስረዱልኛል፤ ወላጅ አባቴ አቶ ደሳለኝ ገደቡ በአቋቋሙት የሽርክና ማህበር ውስጥ የማህበሩ አባል መሆኔንና የድርጅቱን ገቢ በሙሉ ተረክቤ በስሜ ሳስቀምጥ መቆየቴን ከሰነድ ማስረጃው በተጨማሪ ያስረዱልኛል በማለት በመጀመሪያው ጭብጥ 1ኛ ደሳለኝ አያሌው፣ 2ኛ የወንድወሰን አካሉ፣ በሁለተኛው ጭብጥ ደግሞ 1ኛ ደሳለኝ ገደቡ፣ 2ኛ ናዝሬት ደሳለኝ የተባሉን ምስክሮች አቅርቦ አሰምቷል፡፡

በመጀመሪያው ጭብጥ ላይ የተጠሩት ሁለቱም የተከሳሹ መከላከያ ምስክሮች ተመሳሳይ በሆነ ቃል ተከሳሹ በ1982 ዓ.ም በቴፒ ቡና ተክል ልማት ፕሮጀክት ውስጥ በብር 500.00 /አምስት መቶ ብር/ የወር ደመወዝ ተቀጥሮ ሲሰራ በወቅቱ በመ/ቤቱ ውስጥ የሂሳብ ስራ ስለነበር እሱን ለመስራት በየቀኑ ከስራ ሰዓት ውጭ እና ቅዳሜ እና እሁድ ያንን ሂሳብ ከሌሎች ሰራተኞች ጋር በመሆን ይሰራ ስለነበር ለዚህ ለሰራው ስራ የትርፍ ሰዓት ክፍያ ይከፈለው እንደነበር ፕሮርጀክቱ ያለበት ቦታ ከከተማ የራቀ በመሆኑ ፕሮጀክቱ ለሰራተኞች የመኖሪያ ቤት ኪራይ ነፃ ሰጥቷቸው የነበረ እንደሆነና የውሃ እና የመብራት ክፍያ የማይከፍሉ እንደነበር አስረድተዋል፡፡

በሁለተኛ ጭብጥ ላይ 1ኛው የተከሳሹ መከላከያ ምስክር ሲያስረዳ ክልል 6 ውስጥ አሶሳ ከተማ 4800 ካ.ሜ ቦታ ስለነበረኝ ይህንን ቦታ ከማቦዝነው ለምን ከልጆቸ ጋር የብሎኬት ማምረቻ አንከፍትም በማለት ልጆቸን አሰባስቤ ማህበር በ1995 ዓ.ም ከአቋቋምን በኋላ የማምረቻ ማሽኑን ገዝቶ የላከልኝ ተከሳሹ ነው፡፡ ብሎኬቱን በማምረት የምናገኘውን ገቢ የተከሳሹ ታናሽ ወንድም ለስራ ወደ አዲስ አበባ ስለሚመላለስ በየወሩ ወደ አዲስ አበባ ይዞ በመሄዱ በአጋጣሚ ተከሳሹ ለስራ ከባሕር ዳር ወደ አዲስ አበባ ሄዶ ከተገናኙ ለእሱ ካልተገናኙ ደግሞ አዲስ አበባ ለምትኖረው የተከሳሹ ታላቅ እህት ተከሳሹ ወደ አዲስ አበባ ሲመጣ ለእሱ እንድታስረክበው በማለት ስጥቷት ነው

የሚመለስ፤ በአቋቋምነው ማህበር ውስጥ የማህበር አባላት የነበሩት ዳግም፣ ሰናይ፣ ስንዱ፣ ናዝሬት፣ ፍሬሕይወት እና ሰብለ ወንጌል የተባሉ ልጆች ሲሆኑ የብሎኬት ማምረቻው ማምረት ካቆመ በግምት ወደ 10 ዓመት ይሆነዋል በማለት አስረድቷል፡፡

በሁለተኛው ጭብጥ ላይ ሁለተኛዋ የመከላከያ ምስክር ስታስረዳ ደግሞ አሶሳ ከተማ ውስጥ የአባታችን ሰፋ ያለ ቦታ ስላለው በዚህ ቦታ ላይ ለቤተሰቡ መታሰቢያ የሚሆን የብሎኬት ማምረቻ እንድናቋቁም አባታችን ሀሳብ ስላቀረበ በሀሳቡ ተስማምተን አባታችን ብር 150,000.00 /አንድ መቶ ሃምሳ ሽህ ብር/፣ እኛ ደግሞ እንደየአቅማችን ገንዘብ በማዋጣት በ1995 ዓ.ም የሽርክና ማህበር ካቋቋምን በኋላ በአጠቃላይ ሂሳቡን እንድቆጣጠርና የገንዘቡን አቀማመጥና አሰሳሰብ በበላይነት እንዲመራ ተከሳሹን መርጠነዋል፡፡ ማህበሩን ስናቋቁም የማህበሩ አባላት አባታችን፣ እኔ /ናዝሬት/፣ ተከሳሹ፣ ሰናይት፣ ፍሬሕይወት እና መስፍን ነን፡፡ ማህበሩ ተቋቁሞ ማምረቻው ስራ ከጀመረ በኋላ በየጊዜው የምናገኘው ገንዘብ ወጪ እና ገቢው ምን ያህል እንደሆነ አላስታውስም፡፡ ከማህበሩ የሚገኘውን ገንዘብ የሚሰበስብ አባቴ ሲሆን ለተከሳሹም ባሕር ዳር አምጥቶ የሚሰጠው አባቴ ነው፡፡ ማምረቻ ድርጅቱ እስከ አሁን ድረስ ስራ አላቆመም፤ እየሰራ ነው በማለት አስረድታለች፡፡

እኛም የተከሳሹን መከላከያ ማስረጃዎች ከዐ/ሕግ ማስረጃዎች ጋር በማገናዘብ መርምረናቸዋል፡፡ በምርመራው መሰረትም የተከሳሹ የመጀመሪያ መከላከያ ማስረጃ ተከሳሹ ከተቀጠረበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ሰኔ 30 ቀን 2002 ዓ.ም ድረስ ያገኘው የተጣራ ደመወዙ ድምር ብር 337,978.14 /ሶስት መቶ ሰላሳ ሰባት ሽህ ዘጠኝ መቶ ሰባ ስምነት ብር ከአስራ አራት ሳንቲም/ እንደሆነ የሚያስረዳ ነው፡፡ ይህ ማስረጃ የሚያስረዳው ተከሳሹ በመንግስት ሰራተኝነት ተቀጥሮ ለ20 ዓመታት ሲሰራ ያገኘውን የተጣራ ደመወዙን ሲሆን ማስረጃው የሚያሳየው ተከሳሹ በዚህ ጊዜ ውስጥ ያገኘውን የተጣራ አጠቃላይ ደመወዙን እንጅ ለመሰረታዊ ፍላጎቶቹ ማለትም ለምግብ፣ ለልብስና ለመጠለያ እንዲሁም ለቤተሰቦቹ ማስተዳደሪያ ያወጣው ወጪ ምን ያህል እንደሆነ አያስረዳም፡፡ ይህ በሆነበት ሁኔታ ተከሳሹ ገቢውን በማሳየት ገንዘብ ያገኘበትን ምንጭ አስረድቷል ለማለት የሚቻል ሆኖ አላገኘነውም፡፡ የተከሳሹን ሁለተኛውን የሰነድ ማስረጃ ስንመረምረው ተከሳሹ ከኢፌዴሪ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት የካቲት 24 ቀን 2000 ዓ.ም የሂሳብ አዋቂ ሆኖ ለመስራት የሚያስችለው የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተሰጠው መሆኑን እና ይህንን የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት መሰረት አድርጎ የባሕር ዳር ከተማ አስተዳዳር ንግድ ኢን/ኢን/ማስ/ማስ/ጽ/ቤት በብር 25,000.00 /ሃያ አምስት ሽህ ብር/ ካፒታል የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት የሰጠው መሆኑና ይህ የንግድ ምዝገባ ፈቃድ በ2001 ዓ.ም የታደሰ መሆኑን ከሚያስረዳ በስተቀር በዚህ ፈቃዱ መሰረት ስራ ሰርቶ ገቢ ያገኘ መሆኑን የሚያስረዳ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ሶስተኛው መከላከያ ማስረጃ ደግሞ የተከሳሹ ባለቤት በምግብ ንጽህና አገልግሎት እና በቤት ዕቃዎች የንግድ ስራ መስክ በብር 5,000.00 /አምስት ሽህ ብር/ ካፒታል መስከረም 28 ቀን 2002 ዓ.ም የንግድ ስራ ፈቃድ የተሰጣት መሆኑንና ከዚያ በኋላ ያልታደሰ መሆኑን ከሚያሳይ በስተቀር በተሰጣት ፈቃድ መሠረት የንግድ ስራ አከናውና ያገኘችው ትርፍ ምን ያህል እንደሆነ የማያሳይ ከመሆኑ በተጨማሪ በተከሳሹ ላይ ክስ እስከተመሰረተበት ጊዜ ባለው 10 ወር ጊዜ ውስጥ በብር

5,000.00 /አምስት ሽህ ብር/ ካፒታል ብር 105,746.74 /አንድ መቶ አምስት ሽህ ሰባት መቶ አርባ ስድስት ብር ከሰባ አራት ሳንቲም/ የሚደርስ ገቢ ታገኛለች ተብሎ ስለማይገመት ይህ የመከላከያ ማስረጃም ሚዛን የሚደፋ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በአሶሳ ከተማ ውስጥ ነዋሪ የሆኑት ወላጅ አባቴ በአወጡት ንግድ ፈቃድ በሚኖሩበት ከተማ በስማቸው ተመዝግቦ በሚገኘው የይዞታ ቦታቸው 5 ልጆቻቸውን የማህበሩ አባላት በማድረግ በአቋቋሙት የብሎኬት ማምረቻ ድርጅት ውስጥ እኔ በማህበር አባልነቴ የገቢ ምንጭ አገኝ የነበረ መሆኑንና በማህበሩ አባለት ስምምነት በተሰጠኝ ኃላፊነት መሰረት ከብሎኬት ማምረቻ ድርጅቱ የሚገኘውን ገንዘብ በስሜ የማስቀምጥ መሆኔን ያስረዳልኛል በሚል የቀረበውን የሰነድ ማስረጃ ስንመረምረው ደግሞ ማስረጃው በብር 225,000.00 /ሁለት መቶ ሃያ አምስት ሽህ ብር/ ካፒታል የብሎኬት ማምረቻ ለማቋቋም ስድስት አባላት ያሉት የእሽሙር የሽርክና ማህበር ለማቋቋም የመግባቢያ ሰነድ እና የአባላቱን የስራ ኃላፊነት አዘጋጅተው የተፈራረሙ መሆናቸውን የሚያስረዳ ከመሆኑ ባሻገር አንደኛ አባላቱ ሊያዋጡት የተስማሙበትን ብር 225,000.00 /ሁለት መቶ ሃያ አምስት ሽህ ብር/ ካፒታል ማዋጣታቸውን የሚያሳይ የሂሳብ ሰነድ አልቀረበም፤ ሁለተኛው የብሎኬት ማምረቻ መሳሪያውም የተገዛ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ አልቀረበም፤ ሶስተኛ በአባላቱ ለማዋጣት የተስማሙበት ካፒታል ወጥቶ የብሎኬት ማምረቻ መሳሪያው ተገዝቶ ስራ በመስራት ትርፍ ይሰበሰበና በተከሳሹ ስም ይቀመጥ ነበር ቢባል እንኳ ይህ ከብሎኬት ማምረቻው የሚገኘው ገቢ በተከሳሹ ስም መቀመጡን የሚያስረዳ የባንክ ስቴትመንት በማስረጃነት አለመቀመጡ የቀረበውን የሰነድ ማስረጃ ተቀባይነት እንዳይኖረው ከማድረጉ በተጨማሪ ይህንን ማስረጃ ያጠናክራሉ ተብለው የተጠሩት የሰው መከላከያ ምስክሮችን ቃል ከዚህ የሰነድ ማስረጃ ጋር በማገናዘብ ስንመረምረው በዚህ ጭብጥ ላይ የተጠራው 1ኛው የመከላከያ ምስክር ሲያስረዳ ብሎኬቱን በማምረት የምናገኘውን ገቢ የተከሳሹ ታናሽ ወንድም ለስራ ወደ አዲስ አበባ ስለሚመላለስ  በየወሩ ወደ አዲስ አበባ ይዞ በመሄድ በአጋጣሚ ተከሳሹ ለስራ ከባሕር ዳር ወደ አዲስ አበባ ሄዶ ከተገናኙ ለእሱ ካልተገናኙ ደግሞ አዲስ አበባ ለምትኖረው የተከሳሹ ታላቅ እህት ተከሳሹ ወደ አዲስ አበባ ሲመጣ ለእሱ እንድታስረክበው በማለት ሰጥቷት ነው የሚመለስ በማለት የመሰከረ ሲሆን 2ኛዋ የመከላከያ ምስክር ደግሞ ከማህበሩ የሚገኘውን ገንዘብ የሚሰበስብ በአባቴ ሲሆን ለተከሳሹ ባሕር ዳር አምጥቶ የሚሰጠው አባቴ ነው በማለት መመስከሯን እና በዚሁ ጭብጥ 1ኛው የመከላከያ ምስክር የብሎኬት ማምረቻው ማምረት ካቆመ በግምት ወደ 10 ዓመት ይሆነዋል በማለት ሲያስረዳ 2ኛዋ የመከላከያ ምስክር ደግሞ ማምረቻ ድርጅቱ እስከ አሁን ድረስ ስራ አላቆመም፤ እየሰራ ነው በማለት ማስረዳቷ ሲታይ ይህ ማስረጃ ተቀባይነት እንዳይኖረው በበለጠ የሚያጠናክር ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በአወጣሁት የሂሳብ አዋቂነት የንግድ ፈቃድ መሰረት በባሕር ዳር የመጠጥ ውሃና ፍሳሽ አገልግሎት ጽ/ቤት፣ በአማራ መልሶ ማቋቋም ልማት ድርጅት መ/ቤት፣ በእየሩሳሌም ህፃናት ማሳደጊያ ድርጅት እና በአቶ አሊ እንድሪስ የግል ንግድ ድርጅት ሂሳብ በመስራት ገቢ ያገኙሁ መሆኔን ያስረዳልኛል ተብሎ የቀረበውን ማስረጃ ስንመረምረው የባሕር ዳር ውሃ እና ፍሳሽ አገልግሎት ጽ/ቤት በቁጥር ልዩ 2/6058 በቀን 11/04/03 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ ተከሳሹ ከሀምሌ 01 ቀን 1999 ዓ.ም እስከ ሰኔ 30 ቀን 2000 ዓ.ም ድረስ በየወሩ ብር 2,500.00 /ሁለት ሽህ አምስት መቶ

ብር/ እየተከፈለው የጽ/ቤቱን የሂሳብ መዝጋት ስራ የሰራ መሆኑን ያስረዳል፤ የአማራ መልሶ ማቋቋም ልማት ድርጅት መ/ቤት በቁጥር አመልድ/ፓ-1-1-16-12 በቀን 30/09/2003 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ እንዲሁም የእየሩሳሌም ህፃናትና ማህበረሰብ ልማት ድርጅት የባሕር ዳር ማህበረሰብ ልማት ፕሮግራም ጽ/ቤት በቁጥር ባ/ዳ/ማ/ል/ፕ/ጽ/ቤት 5167/2003 በቀን 07/04/2003 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ ተከሳሹ በሁለቱም ጽ/ቤቶች ገንዘብ እየተከፈለው በግሉ የሰራው ስራ አለመኖሩን ገልፀዋል፡፡ በመሆኑም ይህ ማስረጃም ቢሆን ተከሳሹ ከባሕር ዳር ውሃ እና ፍሳሽ አገልግሎት ጽ/ቤት በሰራው የአንድ ዓመት የሂሳብ መዝጋት ስራ ካገኘው ብር 30,000.00 /ሰላሳ ሽህ ብር/ ውጭ ከሌሎች ድርጅቶች ግን ያገኘው ምንም አይነት ገንዘብ እንደሌለ የሚያስረዳ ስለሆነ ተከሳሹ ለተከሰሰበት ምንጩ ያልታወቀ ገንዘብ ማፍራት ወንጀል እንደመከላከያ ሆኖ የሚያገለግል ሆኖ አላገኘነውም፡፡

ስድስተኛው የመከላከያ ማስረጃ ደግሞ ከ1986 ዓ.ም እስከ መጋቢት 1998 ዓ.ም በአማራ ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት ውስጥ በአካውንታንትነት፣ በፋይናንስ አገልግሎት ኃላፊነትና በሂሳብ አማካሪነት በንፅፅር ከሌሎች መ/ቤቶች በተሻለ ደመወዝ የሰራሁ እንደሆነና የድርጅቱን የበርካታ ዓመታት ሂሳብ በቡድን መሪነት የትርፍ ሰዓት ክፍያ እየተከፈለኝ ስሰራ መቆየቴን እና ከ10 ዓመት ላላነሰ ጊዜ ድርጅቱ በሰጠኝ የመኖሪያ ቤት ስኖር የቤት ኪራይ፣ የውሃ እና የመብራት ክፍያ ሳልከፍል መቆየቴ የተሻለ ገንዘብ መቆጠቤን ያስረዳልኛል በሚል የቀረበው ሲሆን ይህ ማስረጃም ተከሳሹ በተራ ቁጥር 1 በጠቀሰው የሰነድ ማስረጃ ስር የሚካተት በመሆኑ እና እኛም ይህንን የሰነድ ማስረጃ ተቀባይነት የለውም በማለት ውድቅ ያደረግነው በመሆኑ ድጋሚ ትንታኔና ምክንያት የሚሰጠው ሆኖ ያላገኘነው ከመሆኑ በተጨማሪ ተከሳሹ ድርጅቱ በሰጠኝ የመኖሪያ ቤት ስኖር የቤት ኪራይ፣ የውሃ እና የመብራት ክፍያ ሳልከፍል ቆይቻለሁ በሚል ያቀረበውም ቢሆን የአማራ ውኃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት በቁጥር አው/00-8/717 በቀን 11/04/2003 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ ተከሳሹ ከሚያዚያ 26 ቀን 1992 ዓ.ም እስከ መጋቢት 1988 ዓ.ም ድረስ ሲሰራ ለተለያዩ ወጭዎች ተብሎ ብር 60.67 /ስድሳ ብር ከስድሳ ሰባት ሳንቲም/ በፔሮል ይቀነስበት እንደነበር የገለፀው ሲታይ ተከሳሹ ከመሰረታዊ ፍላጎቶች ወጭ በተጨማሪ ሌላ ወጭ የነበረበት መሆኑን የሚያስረዳ በመሆኑ ይህ ማስረጃ የዐ/ህግን ማስረጃ ያጠናከራል ካልተባለ በስተቀር ለተከሳሹ ተከላክሎለታል የሚባል ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በ1988 ዓ.ም በማህበር ተደራጅቼ የመኖሪያ ቤቴን ስሰራ ለግንባታው አስፈላጊ የሆኑት ነገሮች ዋጋ አሁን ካለው ዋጋ ጋር ሲነፃፀር በጣም አነስተኛና ዝቅተኛ ስለነበር የቤቱ ግምት ቤቱ በተሰራበት ጊዜ በነበረው ዋጋ ተገምቶ መቅረብ ሲገባው በ2002 ዓ.ም ባለው ዋጋ ተገምቶ መቅረቡ አግባብ ባለመሆኑ በ1988 ዓ.ም የነበረውን የገበያ ዋጋ መሰረት በማድረግ ገለልተኛ በሆነ ባለሙያ ተገምቶ ይቅረብልኝ የሚል ሲሆን ይህንን ዋጋም ገምቶ እንዲያቀረብ የታዘዘው የባሕር ዳር ከተማ አስተዳደር አገልግሎት ጽ/ቤት ተከሳሹ ቤቱን ለማሰራት ያስፀደቀው ዲዛይን ዝርዝር ግምት 163,774.52 /አንድ መቶ ስድሳ ሶስት ሽህ ሰባት መቶ ሰባ አራት ብር ከሃምሳ ሁለት ሳንቲም/ እንደሆነ የሚያስረዳ በመሆኑ ይህንንም ግምት በጥር ወር 2001 ዓ.ም ባለሙያ ገምቶ ሲሰጠው አምኖበት ተቀብሎ የወሰደው ከመሆኑ ባሻገር ለተከሳሹ የግንባታ ፈቃድ የተሰጠው መጋቢት 14 ቀን 2002 ዓ.ም መሆኑ ሲታይ

ደግሞ ተከሳሹ ቤቱን የገነባው ከዚህ ጊዜ በኋላ መሆኑን ግምት ስለሚያስወስድ ከመጋቢት ወር 2002 ዓ.ም በኋላ ያለው ግምት ቢወሰድ ኑሮ የቤቱን ግምት ከፍ ያደርገው ነበር እንጅ ይህ ብቻ ባልሆነ ነበር፡፡ በመሆኑም በዚህ በኩል የቀረበው ማስረጃም ቢሆን የዐ/ህግን ክስ ያጠናክራል ከሚባል ውጭ ተከሳሹን ተከላክሎለታል የሚያሰኝ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

የመጨረሻው የተከሳሹ የሰነድ ማስረጃ ደግሞ ተከሳሹ የፓሊና የፔዳ ቁጥር 1 የቤት ስራ ማህበር አባል ሆኖ እንደማንኛውም አባል በየጊዜው በማዋጣት ባጠራቀመው ገንዘብ የመኖሪያ ቤቱን የመሰረት ግንባታ የሰራ መሆኑን የሚያስረዳ ሲሆን ይህን የሰነድ ማስረጃ ስንመረምረው አንደኛ ይህ ማስረጃ ተከሳሹ በየጊዜው በማዋጣት ያጠራቀመው ገንዘብ ምን ያህል እንደሆነ የሚያስረዳ አይደለም፤ ሁለተኛ ይህ ማስረጃም ቢሆን የሚያስረዳው ተከሳሹ ባጠራቀመው ገንዘብ የመኖሪያ ቤቱን የመሰረት ግንባታ ብቻ የሰራ መሆኑን እንጅ ከመሰረት ግንባታው ውጭ ያለውን የቤት ክፍል የሰራው በምን ገንዘብ እንደሆነ የሚያስረዳ አይደለም፡፡ በመሆኑም ይህ ማስረጃም ተከሳሹን ተከላክሎለታል ማለት የሚቻል ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በቴፒ ቡና ተክል ልማት ድርጅት ከ1983-1985 ዓ.ም ድረስ ለሶስት ዓመታት በሂሳብ ሰራተኛነት ተቀጥሬ ስሰራ ከመደበኛ ደመወዜ በተጨማሪ በሂሳብ መዛግብት ስራ የትርፍ ሰዓት ክፍያ ስለማገኝና ድርጅቱ በሰጠኝ የመኖሪያ ቤት ኪራይ ሳልከፍል በነፃ በመኖሬ የተሻለ ገቢ የነበረኝና ገንዘብ ለመቆጠብ ምቹ ሆኔታ የፈጠረልኝ መሆኑን ያስረዱልኛል በማለት ተከሳሹ አቅርቦ ያስመሰከራቸው መከላከያ ምስክሮች ተከሳሹ በተጠቀሰው ጊዜ በሂሳብ መዛግብት ስራ የትርፍ ሰዓት ክፍያ እየተከፈለው ይሰራ እንደነበርና ለመኖሪያ ቤትም ኪራይ ሳይከፍል የኖረ መሆኑን ቢገልፁም ይህ ይከፈለው የነበረው የትርፍ ሰዓት ክፍያ ምን ያህል እንደነበር በትክክል አላስረዱም፡፡ ምን አልባት ይህ ይከፈለው የነበረው ገቢ ለተከሳሹ መሰረታዊ ፍላጎትቶች ወጭ በቂ ሆኖት በየወሩ ይከፈለው የነበረውን ደመወዙን ያስቀምጥ ነበር ተብሎ ግምት ቢወሰድ እንኳ ይህ በሶስት ዓመት የሚጠራቀመው ገንዘብ ከብር 18,000.00 /አስራ ስምንት ሽህ ብር/ የሚበልጥ ባለመሆኑ ተከሳሹ ለተከሰሰበት የወንጀል ድርጊት መከላከያ የሚሆን አይደለም፡፡

በአጠቃላይ ተከሳሹ የተከሰሰበትን እና በዐ/ህግ ማስረጃዎች የተረጋገጠበትን ምንጩ ያልታወቀ ንብረትና ገንዘብ ማፍራት ወንጀል ባቀረበው የሰነድ ማስረጃና አቅርቦ ባሰማቸው የሰው ምስክሮች ማስተባበል ስላልቻለ ተከሳሹ በተከሰሰበት በወንጀል ሕግ አንቀፅ 419(1)(ለ) ስር የተደነገገውን ተላልፎ የተገኘ ወንጀለኛ ነው በማለት በወ/መ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 149(1) መሠረት የጥፋተኛነት ፍርድ ሰጥተናል፡፡

## <u>የቅጣት አስተያየት</u>

### የዐ/ህግ የቅጣት አስተያየት

- ጥፋተኛ የተባለው ተከሳሽ የወንጀል ድርጊቱን ለመፈፀም የቻለበት ዓላማ ከባድና አደገኛነት ያለው በመሆኑ ምንም እንኳ በቅጣት መመሪያው ላይ ጥፋተኛ የተባለበት የሕግ ድንጋጌ ደረጃ ያልወጣለት ቢሆንም የተፈፀመው ድርጊት ከፍተኛ ጉዳት ያደረሰና አደገኛ በመሆኑ በቅጣት መመሪያው አንቀፅ 19(2) መሠረት ተመጣጣኝ የሆነ ቅጣት እንዲወሰንልን እንጠይቃለን፡፡

- በተጨማሪም ቀደም ሲል በዚሁ ፍ/ቤት የዕግድ ትዕዛዝ የተሰጠባቸው ንብረቶች ማለትም፡-
  1ኛ. በባሕር ዳር ከተማ በቀበሌ 11 ውስጥ በተከሳሹ በራሱ ስም የሚገኘው መኖሪያ ቤት፣
  2ኛ. በባሕር ዳር ከተማ ቀበሌ 13 ውስጥ በተከሳሹ ባለቤት ስም ተመዝግቦ የሚገኘው አንድ መኖሪያ ቤት፣
  3ኛ. በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ባሕር ዳር ቅርንጫፍ በተከሳሹ ስም ተመዝግቦ የሚገኘው ብር፣
  4ኛ. በዳሽን ባንክ ባሕር ዳር ቅርንጫፍ በተከሳሹ ስም ተመዝግቦ የሚገኘው ብር እና
  5ኛ. በዳሽን ባንክ ባሕር ዳር ቅርንጫፍ በተከሳሹ ባለቤት በወ/ሮ ወለላ አየለ ስም ተመዝግቦ የሚገኘው ብር በወንጀል ሕግ አንቀፅ 98(2) እና የሥነ-ምግባር እና ፀረ-ሙስና ኮሚሽን ልዩ የሥነ-ስርዓት ሕግ ቀጥር 434/97 አንቀፅ 29 ላይ በተመለከተው መሠረት ለመንግስት ገቢ እንዲሆን እንዲደረግልን እንጠይቃለን፡፡

የተከሳሹ የቅጣት አስተያየት /በጠበቃው አማካኝነት/

- ተከሳሹ ከአሁን በፊት ሌላ ወንጀል የፈፀመ ስለመሆኑ ሪከርድ አለመቅረቡ እስከ አሁን ድረስ የዘወትር ፀባዩ መልካም የነበረ መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው፡፡ በዐ/ሕግ በኩል ጠቅላላ ወይም ልዩ የቅጣት ማክበጃ ምክንያት አልቀረበም፡፡ ይልቁንም ተከሳሹ ከ20 ዓመት ያላነሰ በመንግስት መስሪያ ቤት ተቀጥሮ በመልካም ስነ-ምግባር ሀገራቸውንና ሕብረተሰቡን ሲያገለግሉ መቆየታቸው፣ በዚህ የአገልግሎት ዘመናቸው ምንም አይነት ጥፋት መፈፀማቸው አለመቅረቡ፣ እንዲሁም በመንግስት ስራ ተቀጥረው በሚያገኙት ደመወዝ አካለ መጠን ያልደረሱ ልጆቻቸውንና ሌሎች ቤተሰቦቻቸውን አስተዳዳሪ መሆናቸውን ቅጣትን ሊያቀሉ የሚችሉ መሆናቸውን ፍ/ቤቱ ግንዛቤ ይዞልን እነዚህን የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች የተከበረው ፍ/ቤት ከአዲሱ የቅጣት ወሰን መጀመሪያ ጋር በማገናዘብ ቅጣቱን በሚያቀል ሁኔታ ውሳኔ እንዲሰጥልኝ፡፡
- በሌላ በኩል ተከሳሹ የተከሰሰ እስከ አሁን ድረስ ያገኘው ከነበረው ገቢ ጋር የማይመጣጠን ገቢ ወይም ንብረቶች ማፍራት የሚል ክስ የተመሰረተ እንጅ ምንም ገቢ ሳይኖራቸው ንብረት ወይም ገንዘብ እንዳፈሩ ክሱ ያልቀረበ ስለሆነ ከገቢያቸው ጋር ተመጣጣኝነቱን በሆነ ሁኔታ ያፈሩት ንብረትና ገንዘብ በሙሉ ለመንግስት ገቢ እንዲሆን በሚል የቀረበው አስተያየት ህጉን መሰረት ያላደረገና ከገቢያቸው ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ንብረት የማፍራት መብታቸውንም ፍ/ቤቱ ተገንዝቦ ለመንግስት ገቢ እንዲሆን የቀረበውን አቤቱታ ውድቅ እንዲያደርግልን እናመለከታለን፡፡

**ቅጣት**

ተከሳሹ ጥፋተኛ የተባለ በወንጀል ሕግ አንቀፅ 419(1)(ለ) ስር የተደነገገውን ተላልፎ ከገቢው ጋር የማይመጣጠን ምንጩ ያልታወቀ ንብረትና ገንዘብ አፍርቶ በመገኘቱ ነው፡፡ ይህ ወንጀል ደግሞ በቅጣት አወሳሰን መመሪያው መሰረት ደረጃ እና እርከን ካልወጣላቸው ወንጀሎች አንዱ ነው፡፡ ምንጩ ያልታወቀ ንብረትና ገንዘብ የማፍራት ወንጀል የንብረቱ መወረስ እንደተጠበቀ ሆኖ በቀላል

እስራት ወይም በመቀጮ ወይም ነገሩ ከባድ ሲሆን ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራትና በመቀጮ የሚያስቀጣ ነው፡፡ እኛም ተከሳሹ ሊቀጣበት ይገባል በማለት የቀላል እስራት ቅጣቱን መርጠነዋል፡፡

የቀላል እስራቱ ቅጣት ለአራት ሲከፈል ደረጃ አንድ ከ10 ቀን እስከ 9 ወር፣ ደረጃ ሁለት ከ9 ወር እስከ 1ዓመት ከ6 ወር፣ ደረጃ ሶስት ከ1 ዓመት ከ6 ወር እስከ 2 ዓመት ከ3ወር እና ደረጃ አራት ከ2 ዓመት ከ3ወር እስከ 3 ዓመት ይሆናል፡፡ ተከሳሹ ህጋዊ ባልሆነ መልኩ ያገኘውን ምንጩ ያልታወቀ ንብረትና ገንዘብ ያፈራው በሰራባቸው የመንግስት መ/ቤቶች ተራ ሰራተኛ እና መካከለኛ በሆነ የኃላፊነት ደረጃ ላይ ተመድቦ በሰራበት ወቅት በመሆኑ እንዲሁም ያገኘው ምንጩ ያልታወቀ ንብረትና ገንዘብም በጣም ከፍተኛ ነው ለማለት የማይቻል ሆኖ ስላገኘነው የተከሳሹ የወንጀል አፈፃፀም በመካከለኛ ደረጃ የሚመደብ ነው፡፡

መካከለኛ ደረጃው የሚያስቀጣ ከ9 ወር እስከ 1 ዓመት ከ6ወር ሲሆን ተከሳሹ የሚቀጣበትን 1 ዓመት መነሻ ቅጣት ይዘን ወደ ነፃነትን የሚያሳጡ የቅጣት እርከኖች ሰንጠረዥ ስንወስደው እርከን 6 ላይ ያርፋል፡፡ በተከሳሹ ላይ የቀረበ የቅጣት ማክበጃ ምክንያት የለም፡፡ በሌላ በኩል ተከሳሹ ከዚህ በፊት የፈፀመው የወንጀል ቅጣት ሪከርድ የሌለበት መሆኑ እና የቤተሰብ አስተዳዳሪ መሆኑ በወንጀል ህግ አንቀጽ 82(1)(ሀ) እና አንቀፅ 86 መሠረት ሁለት ጠቅላላ የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች ናቸው፡፡ በቅጣት አወሳሰን መመሪያው አንቀፅ 16(4) ድንጋጌ መሠረት በቀላል እስራት በሚያስቀጡ ወንጀሎች ቀጥተኛ ለተባለ ወንጀለኛ አንድ የቅጣት ማቅለያ ምክንያት አንድ እርከን ወደታች የሚቀነስለት በመሆኑ በተከሳሹ ላይ የተገኙት ሁለት የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶች ሁለት እርከን ወደታች ስለሚቀንሱለት ተከሳሹ የሚቀጣበት እርከን ወደ እርከን 4 ዝቅ ይላል፡፡

እርከን 4 በቅጣት አወሳሰን መመሪያው መሰረት ከ4 ወር እስከ 7 ወር የሚያስቀጣ ሲሆን ተከሳሹ ያርምና ያስተምረዋል፤ ሌሎችንም ሰዎች ያስጠነቅቃቸዋል በማለት ተከሳሹ ከአሁን በፊት በዚህ ጉዳይ ተይዞ የታሰረበት ጊዜ ካለ በሚታሰብ በ6 ወር ቀላል እስራት ሊቀጣ ይገባል በማለት ልዩነት በሌለው ድምፅ ወስነናል፡፡

ተከሳሹ በባሕር ዳር ከተማ ቀበሌ 13 ውስጥ ግምቱ 163,774.52 የሆነ በስሙ የተመዘገበ አንድ ቪላ የመኖሪያ ቤት፣ በባሕር ዳር ከተማ ቀበሌ 11 ውስጥ በባለቤቱ ስም የተመዘገበ ግምቱ ብር 147,704.14 የመኖሪያ ቤት፡ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ባሕር ዳር ቅርንጫፍ በስሙ የተቀመጠ ብር 101,857.54፣ በዳሽን ባንክ ባሕር ዳር ቅርንጫፍ በስሙ የተቀመጠ ብር 202,108.41 እና በዳሽን ባንክ ባሕር ዳር ቅርንጫፍ በተከሳሽ ባለቤት ስም የተቀመጠ ብር 105,746.74 ሀብትና ንብረት የተገኘበት መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

በሌላ በኩል ተከሳሹ በመንግስት መስሪያ ቤት ለሃያ ዓመታት ተቀጥሮ ሲሰራ ብር 337,978.39፣ ተከሳሹ ከባሕር ዳር ውኃ እና ፍሳሽ አገልግሎት ጽ/ቤት በሰራው የአንድ ዓመት የሂሳብ መዝጋት ስራ ብር 30,000.00 /ሰላሳ ሽህ ብር/፣ እንዲሁም ተከሳሹ በቴፒ ቡና ተክል ልማት ፕሮጀክት ውስጥ በሰራባቸው ሶስት ዓመታት በትርፍ ጊዜው በሰራው የሂሳብ መዝጋት ስራ ያገኝ የነበረውን ገቢ

ለመሰረታዊ ፍላጎቶቹ ማሟያ በማድረግ ደመወዙን ቢያስቀምጥ ብር 18,000.00 ሊያገኝ ይችላል ተብሎ በፍ/ቤቱ ግምት የተወሰደበት ገቢ የነበረው መሆኑ በማስረጃዎች ተረጋግጧል፡፡

በዚህ መሠረት ተከሳሹ የመንግስት ሰራተኛ ሆኖ ለሃያ ዓመታት ሲሰራ ያገኝ የነበረው የወር ደመወዝ በተነፃፃሪ ከሌሎች የመንግስት ሰራተኞች የተሻለ እንደነበር ከቀረበው የዐ/ህግ የሰነድ ማስርጃ መገንዘብ የሚቻል በመሆኑ ይህ ደመወዙ መሰረታዊ ፍላጎቶቹን ከማሟላት በተጨማሪ አንድ የመኖሪያ ቤት ለመስራት አያስችለውም የሚል ግምት ስለሌለን በባሕር ዳር ከተማ ቀበሌ 13 ውስጥ ግምቱ 163,774.52 የሆነ በስሙ የተመዘገበ አንድ ቪላ የመኖሪያ ቤት፣ ከባሕር ዳር ውኃ እና ፍሳሽ አገልግሎት ጽ/ቤት በሰራው የአንድ ዓመት የሂሳብ መዝጋት ስራ ያገኘው ብር 30,000.00 /ሰላሳ ሽህ ብር/ እንዲሁም በቴፒ ቡና ተክል ልማት ፕሮጀክት ውስጥ በሰራባቸው ሶስት ዓመታት በትርፍ ጊዜው በሰራው የሂሳብ መዝጋት ስራ ያገኝ የነበረውን ገቢ ለመሰረታዊ ፍላጎቶቹ ማሟያ በማድረግ ደመወዙን ቢያስቀምጥ ብር 18,000.00 ሊያገኝ ይችላል ተብሎ በፍ/ቤቱ የተወሰደውን ግምት ለራሱ በማድረግ ከዚህ ውጭ ያለው ገንዘብና ንብረት ውርስ ሊሆን ይገባል በማለት ልዩነት በሌለው ድምፅ ወስነናል፡፡

**ትዕዛዝ**

- ይግባኝ መብት ስለሆነ ለጠየቀ ወገን ፍርዱና የቅጣት ውሳኔ ተገልብጦ ይሰጥ፡፡
- ተከሳሹ ላይ የተወሰነውን የእስራት ቅጣት ተከታትሎ እንዲያስፈፅም ለባሕር ዳር ማረሚያ ቤት የማሰሪያ ትዕዛዝ ይፃፍ፡፡
- በባሕር ዳር ከተማ ቀበሌ 11 ውስጥ በተከሳሹ ባለቤት በወ/ሮ ወለላ አየለ ስም የተመዘገበ አንድ የመኖሪያ ቤት፣ በኢትዮጵያ ንግደ ባንክ ባሕር ዳር ቅርንጫፍ በተከሳሹ ስም ከተቀመጠው ብር 101,857.54 ውስጥ ብር 48,000.00 ተቀንሶ በተከሳሹ ሂሳብ ለተከሳሹ እንዲመዘገብ ሆኖ ቀሪው ብር 53,857.54፣ በዳሽን ባንክ ባሕር ዳር ቅርንጫፍ በተከሳሹ ስም የተቀመጠ ብር 202,108.41 እና በዳሽን ባንክ ባሕር ዳር ቅርንጫፍ በተከሳሽ ባለቤት ስም የተቀመጠው ብር 105,746.74 ለመንግስት ገቢ እንዲሆን ለሚመለከታቸው መ/ቤቶች ትዕዛዝ ይፃፍ፡፡
- በተከሳሹ ላይ የነበረው ዋስትና ወርዷል፤ ይፃፍ፡፡
- መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የኮ/መ/ቁ 106020

ነሐሴ 28 ቀን 2004 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሙስጠፋ አህመድ

ዮሐንስ ጌስያብ

ጥዑም ገብሩ

**ከሣሽ**፡- የፌ/የሥ/ም/ፀ/ሙ/ኮ/ዐ/ሕግ አቶ በቃሉ ያለው ቀረቡ

**ተከሣሽ**፡- አቶ ያሬድ ጌታነህ ተ/ኃይማኖት ከማ/ቤት ቀረቡ

የግራ ቀኙ ክርክር እና ማስረጃ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቶአል፡፡

## ፍርድ

የኮሚሽኑ ዐ/ሕግ በ14/06/04 በተፃፈና በፍ/ቤት ትዕዛዝ ተሻሽሎ በቀረበ ማመልከቻ በተከሣሹ ላይ ሁለት ክሶችን የመሠረተ ሲሆን ይዘታቸውም በአንደኛ ክስ ተከሣሹ በኢ.ፌ.ዴ.ሪ የወንጀል ሕግ በአንቀጽ 419 (1)(ሀ) እና (ለ) ሥር የተደነገገውን በመተላለፍ ተከሣሹ ከሰኔ 18 ቀን 1993 ዓ.ም እስከ ሰኔ 9 ቀን 2002 ዓ.ም በተለያዩ የመንግስት መሥሪያ ቤቶች ማለትም በአዲስ አበባ መንገድ ትራንስፓርት መ/ቤት በሂሣብ ፀሐፊነት ብር 285.00 /ሁለት መቶ ሰማኒያ አምስት ብር/ በን/ስ/ላ/ክ/ከተማ ቀበሌ 17 በደንብ አስከባሪነት ብር 950.00 /ዘጠኝ መቶ ሃምሳ ብር/ በየካ ክ/ከተማ ገቢዎች ጽ/ቤት በነገረ ፈጅነት ብር 1,040.00 /አንድ ሺ አርባ ብር/ እንዲሁም በፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በሕግ ረዳትነት ብር 1,200.00 /አንድ ሺ ሁለት መቶ ብር/ እና በዳኝነት ብር 2,150.00 /ሁለት ሽህ አንድ መቶ ሃምሣ ብር/ ደመወዝ እየተከፈለው ሲሰራ የነበረ ሲሆን ከመንግስት መ/ቤቶች ከሚያገኘው ደመወዝ ውጭ ሌላ የገቢ ምንጭ ሣይኖረው ከሚያገኘው ህጋዊ ገቢ ጋር የማይመጣጠን በኦሮሚያ ክልል ሰበታ ከተማ ቀበሌ 03 በካርታ ቁጥር ሰ/6239/99 የተመዘገበ ጅምር ቤት በ16/2/2002 ዓ.ም በባለቤቱ ብርቄ ገለታ ስም በ105,000.00 ብር /አንድ መቶ አምስት ሺ ብር/ ከገዛ በኋላ ግምቱ ብር 554,377.35 /አምስት መቶ ሃምሣ አራት ሺ ሶስት መቶ ሰባ ሰባት ብር ከሰላሳ አምስት ሣንቲም/ የሆነ ቪላ ቤት የሰራ በመሆኑ የሰሌዳ ቁጥሩ ኮድ 2 አ.አ 96146 የሆነ ላንድ ክሮዘር መኪና በ26/4/2003 ዓ.ም በብር 200,000 ብር /ሁለት መቶ ሺ ብር/ የገዛ በመሆኑ እንዲሁም በ28/10/2002 ዓ.ም የሰሌዳ ቁጥር ኮድ 2 አ.አ 99082 የሆነ የቤት መኪና ከገዛ በኋላ በ29/09/2003 ዓ.ም በብር 370,000.00 /ሶስት መቶ ሰባ ሺህ ብር/ የሸጠው ሲሆን ከሽያጩ ያገኘውን ብር 370,000.00 ምንጩ ካልታወቀ ብር 230,000.00 /ሁለት መቶ ሰላሳ ሺህ ብር/ በድምሩ ብር 600,000.00 /ስድስት መቶ ሺህ ብር/ ልደታ ክ/ከተማ ቀበሌ 01 የቤት ቁጥር 999 በሆነውና ከቀበሌው በተከራየው ቤት ውስጥ የተገኘ በመሆኑ በተጨማሪ ሰበታ ከተማ ቀበሌ 03 ውስጥ በሚገኘው የመኖሪያ ቤቱ ውስጥ ብር 45,000 /አርባ አምስት ሺ ብር/ በድምሩ

645,000 /ስድስት መቶ አርባ አምስት ሺ ብር/ ካስቀመጠበት በብርበራ የተገኘ በመሆኑ በፈፀመው ምንጩ ያልታወቀ ንብረትና ገንዘብ ይዞ መገኘት የሙስና ወንጀል ተከሷል፡፡

2ኛ ክስ ወንጀሉ በ1997 ዓ.ም በሥራ ላይ የዋለውን የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የወንጀል ህግ አንቀፅ 684(1) ስር የተደነገገውን በመተላለፍ፡፡ የወንጀሉ ዝርዝር፤-ተከሣሹ በሙስና ወንጀል ተጠርጥሮ በፌዴራል የሥነ ምግባር እና የፀረ ሙስና ኮሚሽን ምርመራ እየተካሄደ ባለበት ወቅት ንብረቱን ከኮሚሽኑ እይታ ውጭ ለማድረግ በማሰብ ምንጩ ባልታወቀ ገንዘብ በ28/10/2002 ዓ.ም የገዛውን የሰሌዳ ቁጥር 2 አ.አ - 99082 የሆነ የቤት መኪና ህገ ወጥ አመጣጡን በመሰወርና ህጋዊ በማስመሰል በ29/9/2003 ዓ.ም በብር 370,000 (ሶስት መቶ ሰባ ሺ ብር) ሙላቷ በየነ ለተባሉ ግለሰብ በሽያጭ ያስተላለፈ በመሆኑ በፈፀመው በወንጀል ድርጊት የተገኘን ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብ የሙስና ወንጀል ተከሷል የሚል ነው፡፡

ተከሣሹ በ26/11/03 በነበረው ችሎት ቀርቦ የክስ ማመልከቻው ደርሶት ከተነበበለት በኋላ ጉዳዩ በመደበኛ የክርክር ሥነ ሥርዓት እንዲመራ በእለቱ በተሰጠው ትዕዛዝ መሠረት ሲጠየቅ የሚያቀርበው መታወቂያ አለመኖሩን በመግለፅ በአንደኛ ክስ የተመለከቱትና በይዞታዬ ሥር የተገኙት ተሽከርካሪ፣ ቢላ ቤት እና ብር 645,000 /ስድስት መቶ አርባ አምስት ሺህ/ ጥሬ ገንዘብ የግል ንብረቶቼ እና በሕጋዊ መንገድ ያገኘኋቸው ስለመሆኑ አስረዳለሁ፤ በሁለተኛ ክስ የተመለከተውን ተሽከርካሪ መሸጤ ትክክል ነው፡፡ የሸጥኩት ግን በክሱ እንደተባለው ኮሚሽኑ ምርመራ መጀመሩን አውቄ ከምርመራው እይታ ለመሰወር በማሰብ አይደለም በማለት ቃሉን ያስመዘገበ ሲሆን ዐ/ሕግም ጉዳዩን በአዳር ካስቀጠረ በኋላ ተከሳሹ በአንደኛ ክስ የተመለከተውን ፍሬ ነገር ያመነ በመሆኑ በክስ ማመልከቻው የምስክሮች ዝርዝር በተ.ቁ 1፣4፣5፣ እና 6 የተጠቀሱትን ምስክሮች መስማት አያስፈልገንም፤ በተ.ቁ 2 እና 3 የተጠቀሱትን ምስክሮች በሁለተኛ ክስ እናሰማለን በማለት አስመዘገበ፡፡ ፍ/ቤቱም ይህንኑ ካገናዘበ በኋላ ተከሣሹ በጠየቀው መሠረት በአንደኛ ክስ መከላከያውን እንዲያሰማ፤የሚያሰማው ግን ዐ/ሕግ በሁለተኛ ክስ ምስክሮቹን ካሰማ በኋላ እንደሆነ ዐ/ሕግ በሁለተኛ ክስ ምስክሮቹን እንዲያሰማ በ27/11/2003 ዓ.ም በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት ሁለቱን ምስክሮች በ30/02/2004 ዓ.ም አቅርቦ አሰምቶአል፡፡

በዚህም መሠረት ወ/ሮ ሙላቷ በየነ የተባሉ 1ኛ ምስክር ከተከሣሹ ጋር የተገናኙት ለነበረባቸው የፍ/ቤት ክርክር የሕግ ባለሙያ ሲያፈላልጉ እንደሆነ፣ የተገናኙትም በ27/04/2003 ዓ.ም እንደሆነ፣ በ26/09/03 ከተከሣሹ ጋር በቢሮው ቀጠሮ እንደነበራቸው፣ ከቀጠሮው ሰዓት ዘግይተው እንደደረሱ፣ የዘገዩት በትራንስፓርት ችግር እንደሆነ እና መኪና እንደሌላቸው እንደነገሩት፣ በዚህ መነሻ ተከሣሹ የሚሸጥ መኪና እንዳለው እንደነገራቸውና በሞባይሉ ላይ ያለውን የመኪናውን ምስል እንዳሳያቸው፣ የሰሌዳ ቁጥሩ 2-99082 እንደሆነ ተነጋግረውና ተስማምተው በ27/09/03 በብር 370,000.00 /ሶስትመቶ ሰባ ሺህ/ እንደገዙት፤ እለቱ ቅዳሜ ስለነበረ ውሉን ሰኞ በ29/09/03 በውልና ማስረጃ ተፈራርመው ባለንብረቱን በ30/09/03 እንዳዛወሩ በውልና ማስረጃ በተፈራረሙት ውል ላይ የግዥ ዋጋው በተከሣሹ አነሳሽነት ብር 150,000 /አንድ መቶ ሃምሳ ሽህ/ ተደርጐ

እንደተፃፈ፣ የብር 370,000.00 ውል እና ቀጥሎም በውልና ማስረጃ ከተፈራረሙ ከሶስት ቀናት አካባቢ በኋላ የብር 225,000 /ሁለት መቶ ሃያ አምስት ሺህ/ ውል እንደተዋዋሉ፣ የብር 225,000 ውል ለመዋዋል የቻሉት የሰው ብድር ስላለብኝ መኪናውን በዚህ ዋጋ እንደሸጥኩ ለማሣየት ፈልጌ ነው በማለት ተከሣሹ ደውሎ በጠየቃቸው መሠረት እንደሆነ፣ የግዥውን ዋጋ የተለያየ አድርገው የፈረሙት ተከሳሹ የሕግ ባለሙያ በመሆኑ ምክንያት እምነት አሳድሮባቸው ስለነበረ እንደሆነ፡ የስም ዝውውሩ ተፋጥኖ እንዲከናወን የጠየቁት እርሳቸው እንደሆኑ፣ ብር 370,000 እና 225,00 የተጠቀሰባቸው ውሎች የተፃፈበትን ቀን በወቅቱ እንዳላስተዋሉ፣ የብር 370,000 ውል የተፃፈው በህዳር ወር 2003 ዓ.ም ተብሎ መሆኑን ያወቁት ፀረ ሙስና ኮሚሽን ተጠርተው ውሉን በተመለከቱበት ጊዜ እንደሆነ፣ ያለብኝን የሰው ዕዳ ለመክፈል ነው ከማለት በስተቀር መኪናውን የሚሸጥበት ሌላ ምክንያት የነበረው ስለመሆኑ ተከሣሹ የነገራቸው ነገር እንደሌለ፣ በውልና ማስረጃ በተደረገው ውል ላይ አቶ አብርሃም በርመጂ እና የተከሣሹ ባለቤት በምስክርነት እንደፈረሙ እቶ አብርሃም የመጡት በእርሣቸው በኩል እንደሆነ በመግለጽ የመሰከሩ ሲሆን አቶ አብርሃም ቢርመጂ የተባሉት 2ኛ ምስክር ከ1ኛ ምስክር ጋር ቤተሰብ እንደሆነ ስለመኪና እውቀት እንዳላቸው፣1ኛ ምስክር መኪና ለመግዛት አስበው እንዲያዩላቸው በጠየቋቸው መሠረት በ27/09/03 ብሔራዊ ትያትር አካባቢ ሄደው ተከሣሹን እንዳገኙት እና ተሽከርካሪውን ተመልክተው ይዞታው ጥሩ እንደሆነ ለ1ኛ ምስክር እንደገለፁ ምስክሩዋም ተስማምተው ገንዘብ ከባንክ አውጥተው ወደ ተከሣሹ ቢሮ አብረው በመምጣት ክፍያ ፈጽመው ሊብሬውን ተረክበው እንደሄዱ በ29/09/03 በውልና ማስረጃ ውሉን በብር 150,000 እንደተዋዋሉ፣ በ30/09/03 ስም እንዳዛወሩ እና በብር 370,000 ውል ላይ እንዳልፈረሙ በመግለጽ መስክረዋል፡፡

የጽሑፍ ማስረጃን በተመለከተ በክስ ማመልከቻው የጽሁፍ ማስረጃ ዝርዝር ከተ.ቁ 1 እስከ 8 የተዘረዘሩት ሰነዶች ቀርበው ለተከሣሹም እንዲደርሱ የተደረገ ሲሆን ፍ/ቤቱም የዐ/ሕግ ክስ እና ማስረጃ እንዲሁም ተከሣሹ ስለቀረበበት አንደኛ ክስ ያስመዘገበውን ቃል ከመረመረ በኋላ በሁለቱም ክሶች መከላከያውን ማሰማት እንዲጀምር በ28/06/04 በነበረው ችሎት በሰጠው ትዕዛዝ መሠረት ተከሣሹ በ03/08/04 በነበረው ችሎት አራት ምስክሮችን አቅርቦ አሰምቷል፡፡

በዚህ መሠረት አቶ ገብሬ ዳዲ የተባሉ 1ኛ የመ/ምስክር የተከሣሹ እናት እና የባለቤታቸው እናት እህትማማቾች በመሆናቸው ከተከሣሹ ጋር የጋብቻ ዝምድና እንዳላቸው የሚኖሩት በኦሮሚያ ክልል በምስራቅ ሸዋ ዞን በአደአ ወረዳ ኡዴ ቀበሌ ውስጥ እንደሆነ፣ ቀበሌው በቢሸፍቱ ከተማ በ12 /አስራ ሁለት/ ኪ.ሜ ርቀት ላይ እንደሚገኝ የሚተዳደሩት በግብርና ሥራ እንደሆነ ተከሣሹ በሰበታ ከተማ አካባቢ የገዛውን ጅምር ቤት ለማስጨረስ ገንዘብ እንዳጠረው ገልጾ ከቤታቸው ድረስ በመምጣት ብር 250,000 /ሁለት መቶ ሃምሳ ሺህ/ እንዲያበድሩት እንደጠየቃቸው ተከሣሹ የጠየቀውን ገንዘብ በመስከረም ወር 2002 በተፃፈ ውል እንዳበደሩት፣ በውሉ ላይ ባለቤታቸው እና ምስክሮች እንደፈረሙ፣ ምስክሩ ወደ አስር ሄክታር አካባቢ የእርሻ ማሳ እንዳላቸው፣ ሁለቱ ሄክታር የራሣቸው ይዞታ ሆኖ ቀሪውን የሚያርሱት ተከራይተው እንደሆነ፣ ከእርሻ ሥራ በተጨማሪ ዶሮ እና ከብት እንደሚያረቡ ወደ 100 /መቶ/ አካባቢ ዶሮዎች እንዳሏቸው፣ የወተት ከብቶች ወደ ስድስት

እንደነበሩዋቸውና አሁን ያሉት ግን ሁለቱ ብቻ እንደሆኑ በዓመት እስከ ብር 150,000 /አንድ መቶ ሃምሳ ሺህ/ ገቢ እንደሚያገኙ ገንዘቡን የሚያስቀምጡት በቤታቸው እንደሆነ በባንክ የማያስቀምጡት ገንዘቡ ተመልሶ ሥራ ላይ ስለሚውል እንደሆነ እና ለተከሣሹ ያበደሩት ብር 250,000 ተቀምጦ የነበረው በቤታቸው እንደሆነ በመግለጽ መስክረዋል፡፡

ወ/ሮ ሙሉነሽ አሰፋ የተባሉ 2ኛ ምስክር የተከሣሹ እናት እንደሆኑ የሰሌዳ ቁጥሩን የማያስታውሱት ሚኒባስ የሥራ መኪና እንደነበራቸው፣ የገዙት አቶ ሣሙኤል ኃ/መስቀል የሚባሉ የልጃቸው ባለቤት በሰጣቸው ብር 265,000 /ሁለት መተ ስድሳ አምስት ሺህ/ በየካቲት ወር 2002 እንደሆነ ሥራው አዋጭ ሆኖ ስላልተገኘ መኪናውን በ2003 በብር 285,000 /ሁለት መቶ ሰማኒያ አምስት ሺህ/ አቶ አለማየሁ ለሚባል ሰው በወኪላቸው በወ/ሮ ብርቄ ገለታ አማካኝነት እንደሸጡ ከሽያጩ ገንዘብ ውስጥ ብር 160,000 /አንድ መቶ ስድስት ሺህ/ የእርሻ ሥራ ጀምሮ ለነበረው አደም ጌታነህ ለተባለው ልጃቸው እንደሰጡ፣ ብር 120,000 /አንድ መቶ ሃያ ሺህ/ ደግሞ ለተከሣሹ እንደሰጡ የሰጡት በጥቅምት ወር 2003 እንደሆነ ሊሰጡት የቻሉትም ተከሣሹ እግሩን ስለሚያመውና የነበረውን አነስተኛ ተሽከርካሪ ሸጦ በኮረኮንች መንገድ ጭምር ሊያገለግል የሚችል የተሻለ ተሽከርካሪ የመግዛት ሃሣብ እንዳለው ስለነገራቸው እንደሆነ በዚሁ መሠረት ተከሣሹ ገዛሁ ያለውን መኪና አሳይቷቸው እንደነበረ ገንዘቡን የሰጡት በብድር ደንብ ተነጋግረው ሣይሆን ሰርቶ ይመልስልኛል የሚል እምነት ኖሮአቸው እንደሆነ ሣሙኤል ኃ/መስቀል እና የልጃቸው ልጅ የሆነችው ባለቤቱ ራሄል ጌታነህ አንድ ልጅ እንዳላቸው ራሄል አዲስ አበባ ውስጥ ተከራይታ እንደምትኖር ሣሙኤል የሚኖረው አሜሪካን ሀገር እንደሆነ እና ገንዘቡን በታህሳስ ወር 2002 አዲስ አበባ ውስጥ በእጅ እንደሰጣቸው በመግለጽ መስክረዋል፡፡

አቶ ንጉሴ ሀሰን የተባሉ 3ኛ ምስክር የሚተዳደሩበት በግንበኝነት ሙያ እንደሆነ፣ ተከሣሽ ሰበታ አካባቢ ወለቴ በሚባል ቦታ የሚገኝ መሠረቱ የተጀመረ ቤት እንዲሰሩላቸው በመስከረም ወር 2002 ዓ.ም እንደጠየቃቸውና ፕላኑን እንዳሳያቸው ዋጋ አውጥተው እንደነገሩት የግንበኝነት እና የአናፂነት ሥራን ጨምሮ ለቤቱ ሥራ በብር 25,000 /ሃያ አምስት ሺህ/ ለአጥሩ ደግሞ በብር 10,000 /አስር ሺህ/ የእጅ ዋጋ እንደተስማሙና እንደሰሩ ቤቱ 72 /ሰባ ሁለት/ ቆርቆሮ፣ 2700 /ሁለት ሽህ ሰባት መቶ/ ብሎኬት፣ አራት መኪና አሸዋ 130 /መቶ ሰላሳ/ ኩንታል አካባቢ ሲሚንቶ አጥሩ ደግሞ አምስት መኪና ድንጋይ እና 150 ብሎኬት እንደጨረሰ ግብአቶቹ የተገዙበትን ዋጋም ሆነ የቤቱን አጠቃላይ የዋጋ ግምት እንደማያውቁ በመግለጽ መስክረዋል፡፡

አቶ ታደሰ ሰንበቶ የተባሉ 4ኛ እና የመጨረሻ ምስክር ለተከሣሹ እናት አጐት እንደሆኑ የሚተዳደሩት በሞጆ ወረዳ ሞሞሽኬ በሚባል ቀበሌ በግብርና ሥራ እንደሆነ ተከሣሹ ቤት ሰርቼ እግሬን ስለሚያመኝ የመኪና መግዣ አጣሁ ገንዘብ አበድረኝ በማለት በግንቦት ወር 2002 እንደጠየቃቸው እና እርሳቸውም ሰኔ ወር 2002 ብር 250,000 /ሁለት መቶ ሃምሳ ሺህ/ በብድር እንደሰጡት የጽሁፍ ውል እንዳደረጉ የራሳቸው የሆነ ሶስት ሄክታር እና በኪራይ ደግሞ እስከ አምስት ሄክታር መሬት እንደሚያርሱ ከእርሻ ሥራ በተጨማሪ እስከ 15 /አስራ አምስት/ እና 20 /ሃያ/ ከብት

እንደሚያደልቡ፣ ያበደሩት በዓመት ሊመልስላቸው እንደሆነ ውሉን የፃፈው ልጃቸው እንደሆነ መኖሪያቸው ከሞጆ ከተማ በእግር የሁለት ሰዓት መንገድ እንደሆነ የባንክ አገልግሎት እንደማይጠቀሙ የማይጠቀሙትም የሚያገኙት ገንዘብ በአጭር ጊዜ ውስጥ ተመልሶ ለቀጣይ ሥራ ስለሚውል እንደሆነ እና ለተከሣሹ ያበደሩት ገንዘብ ተቀምጦ የነበረው በቤታቸው እንደሆነ በመግለጽ መስክረው የሰው መከላከያ በዚሁ የተጠናቀቀ ሲሆን ተከሣሹ በ17/07/04 ከተፃፈ መግለጫ ጋር የተለያዩ የጽሁፍ ማስረጃዎችን አቅርቦ ዐ/ሕግ በ16/08/04 የተፃፈ የማስተባበያ አስተያየት ሰጥቶባቸዋል፡፡

በመጨረሻም ተከሣሹ በ24/08/04 የተፃፈ የክርክር ማቆሚያ ንግግር አቅርቦ አጠቃላይ ክርክሩ በዚሁ የተጠናቀቀ ሲሆን የዐ/ሕግን ክስ እና ማስረጃ ተከሣሹ በመከላከያው ያስተባበለ መሆን አለመሆኑን ፍ/ቤቱ እንደሚከተለው መርምሮአል፡፡

በዚህም መሠረት በወ/ሕ/አ/ 419(1) (ሀ) እና (ለ) ሥር የተደነገገውን በመተላለፍ ምንጩ ያልታወቀ ሀብት ይዞ ተገኝቶአል በማለት በተከሣሹ ላይ ያቀረበውን አንደኛ ክስ ለማስረዳት ዐ/ሕግ ካቀረበው የጽሁፍ ማስረጃ መካከል በመንግስት ሥራ ያገኝ የነበረውን ገቢ በተመለከተ የተከሣሹ የወር ደመወዝ፡-

1. በአዲስ አበባ መንገድ ትራንስፓርት መ/ቤት ከ18/10/93 እስከ 30/04/94 ድረስ በሂሳብ ፀሐፊነት በሰራበት ጊዜ ብር 285 የነበረው መሆኑን፣
2. በን/ስ/ላ/ክ/ከተማ በቀበሌ 17 ከ01/05/94 እስከ 30/02/96 ድረስ በደንብ አስከባሪነት በሰራበት ጊዜ በክስ ማመልከቻው ላይ ደመወዙ ብር 950 ተብሎ የተገለፀ ቢሆንም በቀረበ የጽሁፍ ማስረጃ መሠረት ግን ብር 450 የነበረ መሆኑን፣
3. በየካ ክ/ከተማ ገቢዎች ጽ/ቤት ከ01/03/96 እስከ 30/01/98 ድረስ በነገረ ፈጅነት በሰራበት ጊዜ ብር 1040 የነበረ መሆኑን፣
4. በፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት ከ01/11/98 እስከ 25/10/99 ድረስ በሕግ ረዳትነት በሰራበት ጊዜ ብር 1200 የነበረ መሆኑን እና፣
5. በፌ/የመ/ደ/ፍ/ቤት በ26/10/99 እስከ 09/10/02 ድረስ በዳኝነት በሰራበት ጊዜ ብር 2,150 የነበረ መሆኑን የሚገልፁ ማስረጃዎች የሚገኙበት ሲሆን በተከሣሹ ይዞታ የተገኘ ምንጩ ያልታወቀ ነው ተብሎ በክሱ ማመልከቻ ላይ የተገለፀው ደግሞ በጥሬ ገንዘብ ብር 645,000 በንብረት ደግሞ ብር 754,377.35 በድምሩ ብር 1,399,377.35 /አንድ ሚሊዮን ሶስት መቶ ዘጠና ዘጠኝ ሺህ ሶስት መቶ ሰባ ሰባት ከ35/100/ ዋጋ ያለው ሐብት ነው፡፡

ተከሣሹ በይዞታው ተገኝቶአል የተባለው ገንዘብና ንብረት የራሱ መሆኑን አምኖ ነገር ግን ገንዘብና ንብረቱ ዐ/ሕግ እንደገለፀው ምንጩ ያልታወቀ ሣይሆን የታወቀ እና ሕጋዊ መሆኑን በመከላከያው እንደሚያስረዳ ገልጾ የሰው እና የጽሁፍ ማስረጃ ካልቀረበባቸው የመከላከያ ነጥቦች መካከል፡-

1. አቶ ገብሬ ዳዲ ከተባሉ ግለሰብ ብር 250,000 እና አቶ ታደሰ ሰንበቱ ከተባሉ ግለሰብ ብር 250,000 በብድር ወስጃለሁ በማለት ተከሣሽ ያቀረበውን የክርክር ነጥብ በተመለከተ የመ/ምስክሮቹ በግብርና ሥራ የሚተዳደሩ ሆነው የሚኖሩት የባንክ አገልግሎት ከሚገኝበት ቦታ በቅርብ ርቀት መሆኑን የገለፁ በመሆኑ ለአንድ ዓመት በብድር ሊሰጥ የሚችል ብር 250,000 ተቀማጭ ገንዘብ ያለው ሰው ደግሞ ገንዘቡን በባንክ ማስቀመጡ የተለያዩ ጠቀሜታ እንደሚሰጠው የሚታወቅ ሆኖ እያለ ምስክሮቹ ገንዘቡን በየቤታቸው ያስቀምጡ እንደነበር መግለፃቸው እና በሌላ በኩል ደግሞ በብድር የሚሰጥ ይህን ያህል ገንዘብ ካላቸው የባንክ አገልግሎት ለምን እንዳልተጠቀሙ ተጠይቀው ገንዘቡ በእጃቸው ብዙ ስለማይቆይና መልሰው በሥራ ላይ ስለሚያውሉት እንደሆነ መግለፃቸው ሲታይ የምስክርነት ቃላቸውን እምነት እንዳይጣልበት የሚያደርገው በመሆኑ በዚህ ነጥብ የቀረበው መከላከያ ተቀባይነት ሊኖረው የሚገባ ሆኖ አልተገኘም፡፡
2. በመንግስት ሥራ ከተቀጠርኩበት ከሰኔ ወር 1990 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ለቀቅሁበት ሰኔ ወር 2002 ዓ.ም ድረስ ባሉት 12 ዓመታት በየወሩ ሲከፈለኝ የነበረውን ደመወዝ እና አበል በሙሉ ሳጠራቀም ነበረ በማለት ተከሣሹ ያቀረበውን የክርክር ነጥብ በተመለከተ በመከላከያ መግለጫው ላይ ከገለፀው ገቢ መካከል ከውትድርና አገልግሎት ሲሰናበት ከታህሳስ 1993 ጀምሮ የብር 167.70 የጡረታ አበል ተወስኖለት የነበረ ስለመሆኑ በጡረታ መለያ ቁጥር ወ/630572 የተሰጠውን የመታወቂያ ወረቀት ከማቅረብ በስተቀር የብር 19,184.00 /አስራ ዘጠኝ ሺህ አንድ መቶ ሰማኒያ አራት/ የጡረታ አበል በርግጥም የተቀበለ ስለመሆኑ ያቀረበው ማስረጃ አለመኖሩ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የመንግስት ሠራተኛ በየወሩ ከሚያገኘው ደመወዝ እና ሕጋዊ ገቢ ላይ ለክፋ ቀን በሚል አቅሙ በፈቀደው መጠን የተወሰነ ገንዘብ ሊቆጥብ እንደሚችል በተለመደው ማህበራዊ ኑሮ የሚታወቅ ቢሆንም ተከሣሹ በየወሩ ያገኝ የነበረውን ደመወዝና አበል እንዳለ ያስቀምጥ እንደነበር ከመግለጽ በስተቀር በማህበራዊ ኑሮ በተለመደው አግባብ መሠረት በየወሩ ወይም በየተወሰነው ጊዜ ይቆጥብ ስለነበረው የገንዘብ መጠን ያቀረበው ክርክር የለም በመሠረቱ ተከሣሹ የተማረ እና በአዲስ አበባ ከተማ የሚኖር የመንግስት ሠራተኛ እንደመሆኑ መጠን ከወርሐዊ ደመወዝ እና ሕጋዊ ገቢው የሚቆጥበውን ገንዘብ ያስቀምጣል ተብሎ የሚገመተው እንደማንኛውም ሌላ የመንግስት ሠራተኛ በባንክ በቁጠባ ማህበር ወይም በመሰል ተቋማት ሲሆን ተከሣሹ ገንዘቡን ያስቀምጥ የነበረው የት እንደሆነ በመኖሪያ ቤቱ ከሆነም የዚህ ዓይነቱን አማራጭ ለምን መከተል እንደመረጠ ያቀረበው ክርክር የለም የተከሣሹ ወላጅ እናት የተከሣሹን እና የቤተሰቡን የኑሮ ወጪ ለመሸፈን የሚያስችል የተለየ እና የተትረፈረፈ ገቢ ወይም ሐብት እንዳላቸው ባልተገለፀበትና ማስረጃ ባልቀረበበት ሁኔታ ተከሣሹ የምኖረው ከእናቴ ጋር በአንድ ግቢ ስለነበር በቀለብ ረገድ ወጪ አልነበረብኝም ለማለት ያቀረው ክርክር ምክንያታዊ ካለመሆኑም በላይ ከቀለብ ውጭ ያሉትን ለእርሱና ለቤተሰብ የሚያስፈልጉ የተለመዱ እና የማይቀሩ ሌሎች ወጪዎችን በተመለከተ ያቀረበው ክርክር የለም ተከሣሹ በማህበራዊ ኑሮ ልማድ መሠረት ከደመወዙ በየወሩ የተወሰነ መጠን በመኖሪያ ቤቱም

ቢሆን ይቆጥብ የነበረ ስለመሆኑ ያቀረበው ክርክር በሌለበት ሁኔታ ፍ/ቤቱ የማህበራዊ ኑሮ ልማድን ብቻ መሠረት በማድረግ ተከሣሽ በየወሩ ገንዘብ ይቆጥብ እንደነበር ግምት መውሰድ የሚችልበት አግባብ አልተገኘም በመንግስት ሥራ ከተቀጠርኩበት ጊዜ ጀምሮ እስከለቀቅሁበት ጊዜ ድረስ ይከፈለኝ የነበረውን ደመወዝ አበል በሙሉ አስቀምጥ ነበር በማለት ተከሣሹ በደፈናው ያቀረበው ክርክር ደግሞ ሊታመን የሚቻል አይደለም በመሆኑም የመከላከያ ነጥቡን ፍ/ቤቱ አልተቀበለውም፤

3. ከጥብቅና አገልግሎት በ2003 ዓ.ም. በብር 266,000/ሁለት መቶ ስድሳ ስድስት ሺህ/ ገቢ አግኝቻለሁ በማለት ተከሣሹ ያቀረበውን የክርክር ነጥብና ማስረጃ በተመለከተ ይህን ያክል ገቢ ማግኘቱ ለገቢዎች ጽ/ቤት የገለፀውና የገቢ ግብር የከፈለበት ክሱ ከተመሰረተበት በኋላ በመሆኑ ምክንያት ገቢው በትክክል ከጥብቅና አገልግሎት የተገኙ መሆኑን ማረጋገጥ የሚቻልበት ሁኔታ ካለመኖሩም በላይ ተከሳሹ የጥብቅና ውሎቹን ያላቀረበ የጥብቅና አገልግሎቱ የተሰጠባቸውን ፍ/ቤቶች እና መዛግብት ያልጠቀሰ እና ገቢው የተገኘው ከሕግ ምክር አገልግሎት ብቻ ነው የሚባል ከሆነም ምክሩን ከሰጣቸው ባለጉዳዮች መካከል የተወሰኑትንም ቢሆን አቅርቦ ለማሰማት ያልደፈረ በመሆኑ መከላከያውን ፍ/ቤቱ እምነት ሊጣልበት የሚችል ሆኖ አላገኘውም፡፡

4. ለክሱ ምክንያት ከሆኑት መካከል የሰ.ቁ. 2-99082 የሆነውን ተሽከርካሪ የገዛሁት በብር 265,000 የሸጥኩት ደግሞ በብር 370,000 መሆኑን ዐ/ሕግ ያቀረበው ማስረጃ ራሱ የሚያመለክት በመሆኑ በሁለቱ ዋጋዎች መካከል ያለው ልዩነት ብር 105,000 ሕጋዊ ገቢ ወይም ትርፍ ተደርጐ ሊወሰድልኝ ይገባል በማለት ተከሣሽ ያቀረበውን ክርክር በተመለከተ በሙስና ወንጀል ከተገኘ ንብረት የተፈራ ሐብት በሙስና ወንጀል የተገኘው ንብረት አካል ተደርጐ እንደሚወሰድ ከፀረ ሙስና ልዩ ሥነ ሥርዓት አዋጅ ከአንቀጽ 34/1/ ድንጋጌ መገንዘብ የሚቻል በመሆኑ የክርክር ነጥቡ ተከሣሹ ተሽከርካሪውን ያገኘው በሙስና ወንጀል ነው ወይስ አይደለም? ለሚለው መሠረታዊ ጭብጥ በሚሰጠው ውሣኔ እልባት የሚያገኝ ይሆናል፡፡

5. ከተያዘው ብር 600,000 ውስጥ ብር 230,000 /ሁለት መቶ ሰላሳ ሺህ/ የወንድሜ የአቶ አደም ጌታነህ ነው በማለት ተከሣሹ ያቀረበውን የክርክር ነጥብ በተመለከተ ተከሣሽ በ26/11/03 በነበረው ችሎት ቀርቦ ሲጠየቅ ብር 645,000 ውን ጨምሮ በክሱ የተጠቀሰው ገንዘብና ንብረት በሙሉ የግል ንብረቱ መሆኑን በማረጋገጥ ገንዘብና ንብረቱን ያገኘው ከሕጋዊ ምንጭ መሆኑን እንደሚያስረዳ ገልጾ እያለ በመከላከያ ደረጃ ወደ ኋላ ተመልሶ ብር 230,000 የወንድሜ ገንዘብ ነው በማለት ተከሣሹ ያቀረበውን ክርክር ፍ/ቤቱ ተቀባይነት ሊኖረው የሚገባ ሆኖ አላገኘውም፤

6. ብር 120,000 /አንድ መቶ ሃያ ሺህ/ ከእናቴ ከወ/ሮ ሙሉነሽ አሰፋ የወሰድኩት ነው በማለት ተከሣሹ ያቀረበውን ክርክር በተመለከተ የተከሣሹ 2ኛ የመ/ምስክር ሆነው የተሰሙት ወ/ሮ ሙሉነሽ አሰፋ የተከሣሽ እናት መሆናቸውን ገልፀሙ የራሣቸው የሆነ

ተሽከርካሪ በሸጡበት ጊዜ ተከሣሹ የነበረውን ተሽከርካሪ ሸጦ የተሻለ በኮረኮንች መንገድ መሄድ የሚችል ተሽከርካሪ ለመግዛት እንደሚፈልግ ገልጾ በጠየቃቸው መሠረት ብር 120,000 የሰጡት መሆኑን መስክረዋል በስማቸው ተመዝግቦ የነበረውን ተሽከርካሪ በብር 285,000 /ሁለት መቶ ሰማኒያ መስት ሺህ/ የሸጡ ስለመሆኑም በ04/02/03 የተፃፈ የሽያጭ ውል ተከሣሹ በመከላከያ ማስረጃነት ያቀረበ ሲሆን ዐ/ሕግ በተከሣሹ የጽሁፍ ማስረጃ ላይ በ16/08/04 በተፃፈ ማመልከቻ አስተያየት በሰጠበት ወቅት የሽያጭ ውሉን አስመልክቶ የቀረበው የማስተባበያ ሃሳብ የለም በመሆኑም ይህ ብር 120,000 /አንድ መቶ ሃያ ሺህ/ ለተከሣሹ እንደ ሕጋዊ ገቢ ሊያዝለት የሚገባ መሆኑን ፍ/ቤቱ ተገንዝቦአል፡፡

7. ባለቤቱ ወ/ሮ ብርቄ ገለታ ከደመወዝ እና ከስንብት ክፍያ ያገኘችው በድምሩ ብር 36,850.70 /ሰላሳ ስድስት ሺህ ስምንት መቶ ሃምሳ ከ70/100/ ሕጋዊ ገቢያችን ነው በማለት ተከሣሹ ያቀረበውን ክርክር በተመለከተ ተጠቃሿ በወርልድ ቪዥን ኢትዮጵያ ተቀጥራ የነበረ መሆኑን እና የሥራ ውሏ ሲቋረጥም የሰንብት ክፍያ የተፈፀመላት መሆኑን የሚገልጽ ደብዳቤ ተከሣሹ በማስረጃነት አቅርቦአል በማስረጃው ላይ ዐ/ሕግ ያቀረበው ማስተባበያ ካለመኖሩም በላይ ገቢው የተገኘው ከሕጋዊ ምንጭ እንደሆነ የተረጋገጠ በመሆኑ እና የጋራ እንደሆነ ግምት የሚወስድበት በመሆኑ በሕጋዊ ገቢነት ሊወሰድ የሚገባው ሆኖ ተገኝቶአል፡፡

ሲጠቃለል በአንደኛ ክስ ተከሣሹ ይዞ ተገኝቶአል ከተባለው የብር 1,399,377.35 ምንጩ ያልታወቀ ንብረት እና ገንዘብ መካከል ከላይ በተ.ቁ 6 እና 7 የተጠቀሰው በድምሩ ብር 156,850.70; አንድ መቶ ሃምሳ ስድስት ሺህ ስምንት መቶ ከ70/100) ያገኘው ከታወቀ ሕጋዊ ምንጭ መሆኑን በመከላከያው ከማስረዳቱ እና ይህ የገንዘብ መጠን በይዞታው ከተገኘው ብር 645,000 ላይ ተቀናሽ መደረግ የሚገባው ከመሆኑ በስተቀር ቀሪውን ገንዘብና ንብረት ያገኘው ከታወቀ ሕጋዊ ምንጭ መሆኑን በመከላከያው ማስረዳት የቻለ ሆኖ አልተገኘም፡፡

ተከሣሹ በወ/ሕ/አ 684(1)ሥር የተከሰሰበትን እና ይከላከል የተባለበትን ሁለተኛ ክስ በተመለከተ በክሱ የተጠቀሰውን የሰ.ቁ 2-99082 የሆነውን ተሽከርካሪ በ29/09/03 በብር 370,000 በሽያጭ ማስተላለፉ ተረጋግጧል፡፡ ተከሣሹም ተሽከርካሪ ውን መሸጡን ሣይክድ ነገር ግን የሸጥኩት ከፀረ ሙስና ኮሚሽኑ እይታ ውጭ ለማድረግ በማሰብ አይደለም በማለት ተከራክሮአል፡፡ በጉዳዩ የቀረቡት የዐ/ሕግ ምስክሮችም ተከሣሹ ተሽከርካሪውን የሸጠው በመደበኛ ሁኔታ እና ግንኙነት መሆኑን ከማረጋገጥ በስተቀር በክሱ እንደተገለፀው ምርመራ የተጀመረበት መሆኑን አውቆ እና ከኮሚሽኑ እይታ ለመሰወር ሰማሰብ ነው የሚል ግምት ለመውሰድ የሚያስችል ሁኔታ ስለመኖሩ የገለጹት ነገር የለም፡፡ ተከሣሹ ተሽከርካሪውን የገዛሁበት ገንዘብ ያፈራሁት ከሕጋዊ ምንጭ ነው በማለት በአንደኛ ክስ መከላከያ ከማቅረብ በስተቀር ሁለተኛ ክስን በተመለከተ ነጥሎ ያቀረበው መከላከያ የሌለ ቢሆንም በሁለተኛ ክስ የተመለከተው እና መፈፀሙ የተረጋገጠው ድርጊት በድንጋጌው የተመለከተውን ወንጀል የሚያቋቁም ነው ወይስ አይደለም የሚለው የሕግ ነጥብ መጤን የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በዚህ መሠረት የወ/ሕ/አ 684(1) በወንጀልነት የደነገገው በሙስና ወንጀል አማካይነት የተገኘን ገንዘብ ወይም ንብረት ሕገወጥ አመጣጥ ሰውሮ በጥቅም ወይም በስራ ላይ በማዋል፣ በማዛዋወር ወይም በማስተላለፍ ሕጋዊ አስመስሎ ማቅረብን ሲሆን በክስ ማመልከቻው አነጋገር መሠረት ተከሣሹ በሙስና ወንጀል አግኝቷል የተባለው በ29/09/03 በሽያጭ ያስተላለፈውን ተሽከርካሪውን ራሱን ሳይሆን ቀደም ሲል ይህንኑ ተሽከርካሪ በ28/10/02 የገዛበትን ጥሬ ገንዘብ ነው፡፡ በድንጋጌው አነጋገር መሰረት ተከሳሹ ተጠያቂ ሊደረግ ይችል የነበረው በሙስና ወንጀል ያገኘውን ገንዘብ ሕገወጥ አመጣጥ ሰወሮ ተሽከርካሪውን ገዝቶአል የሚል ክስ ቀርቦበት ቢሆን ኖሮ ነው፡፡ ይሁን እንጅ በዚህ ረገድ የቀረበበት ክስ የለም፡፡ በተከሣሹ መፈፀሙ የተረጋገጠው ድርጊት በአንቀጽ ከተደነገገው የተለየ ከሆነ ደግሞ በወ/ሕ/አ/ 2(3) እንደተመለከተው በሕግ ላይ ከተደነገጉት ወንጀሎች ጋር ይመሳሰላል በማለት ወንጀልነቱ በግልጽ ያልተደነገገን ድርጊት ወይም ግድፈት ፍ/ቤቱ እንደወንጀል ሊቆጥረው አይችልም፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆ ኖ በከሣሹ ይዞታ ከተገኘው ብር 645,000 ውስጥ ብር 370,000 የዚሁ ተሽከርካሪ የሽያጭ ገንዘብ መሆኑ በአንደኛ ክስ ውስጥ ተመልክቷል በመሆኑም ተከሣሹ በሁለት ክስ በተመለከተው ወንጀል ጥፋተኛ ሊባል የሚቻልበት አግባብ አልተገኙም፡፡

ከላይ የሰፈረው ገንዘብ በማጠቃላል ተከሣሹ በአንደኛ ክስ በወ/ሕ/አ 419(1)(ለ) ስር የተደነገገው በመተላለፍ ባደረገው ምንጩ ያልታወቀ ንብረት እና ገንዘብ ይዞ የመገኘት የሙስና ወንጀል ጥፋተኛ ነው፡፡

በሁለተኛ ክስ በወ/ሕ/አ/ 684(1) ስር የተደነገገው በመተላለፍ አድርጐአል ተብሎ በተከሰሰበት በወንጀል ድርጊት የተገኘን ገንዘብ ወይም ንብረት ሕጋዊ አስመስሎ የማቅረብ የመስና ወንጀል ጥፋተኛ አይደለም በማለት ፍ/ቤቱ በወ/መ/ህ/ሥ/ሥ/ቁ 149(1) መሠረት ወስኗል፡፡

## የቅጣት ውሳኔ

በወንጀል ጉዳይ ጥፋተኛ ሆኖ በተገኘው ሰው ላይ ቅጣት ሊወሰን የሚገባው በወንጀል ሕጉ የተመለከቱ የቅጣት አወሳሰን ደንቦችን መሠረት በማድረግ የቅጣት ማከበጃ ማቅለያ ምክንያቶች መኖር አለመኖራቸውን በማጤን እና በማመዛዘን፣ የቅጣት አወሳሰን መመሪያውን መሠረት በማድረግ እና በአጠቃላይ በአጥፊው ላይ የሚጣለው ቅጣት በአንቀጽ 1 ላይ የተመለከተውን የወንጀል ሕጉን ዓላማ ግብ ሊያሳካ የሚችልበትን አቅጣጫ በመከተል መሆኑ ይታወቃል፡፡

ተከሳሽ ጥፋተኛ የተባለበት የወ/ሕ/አ/419(1) ቀላል እስራትን ወይም መቀጮን ወይም ነገሩ ከባድ ሲሆን ከአምስት ዓመት የማይበልጥ ጽኑ እስራትን እና መቀጮን የሚደነግግ ሲሆን የኮሚሽኑ ዐ/ሕግ በ28/12/04 በተፃፈ ማመልከቻ ወንጀሉ ደረጃ ካልወጣላቸው ውስጥ የሚመደብ በመሆኑ ምክንያት የቅጣት አወሳሰኑ የሚመራው በቅጣት አወሳሰን መመሪያው አንቀጽ 13 መሠረት መሆኑን ተከሳሹ ምንጩ ያልታወቀውን ገንዘብና ንብረት ያፈፈራው በዳኝነት ተሹሞ ይሰራ በነበረበት ጊዜ ጭምር መሆኑን ይዞታ የተገኘው ምንጩ ያልታወቁ ገንዘብና ንብረት ግምትም ከፍተኛ የሚባል መሆኑን እነዚህ ሁኔታዎችም በክብደቱና በአፈፃፀሙ ወንጀሉን በከባድ ደረጃ መመደብ የሚያስችሉ መሆኑን እና በወ/ሕ/አ/108 ላይ የተመለከተውን መስፈርት የሚያሟሉ በመሆኑ ምክንያት በተከሳሹ

ላይ ለሚጣለው ቅጣት መሠረት ተደርጐ መያዝ የሚገባው የጽኑ እሥራት አማራጭ መሆኑን በዝርዝር በመግለጽ በከባድ ደረጃ ለተመደበ ወንጀል በቅጣት አወሳሰን መመሪያው በተቀመጠው ፍቅድ ስልጣን መሠረት ተገቢው ቅጣት እንዲጣልበት እና ምንጩ እንዳልታወቀ በጥፋተኛነት ውሳኔው ላይ በተገለፀው ገንዘብና ንብረት ላይ የውርስ ትዕዛዝ እንዲሰጥለት ጠይቋል፡፡

ተከሳሽ በበኩሉ በ30/12/04 በተፃፈ ማመልከቻ ይዘህ ተገኝተሀል የተባለው ምንጩ ያልታወቀ ገንዘብና ንብረት ከፍተኛ ነው መባሉ ብቻውን የወንጀሉ ደረጃ ከከባድ ለመመደብ የሚያበቃ አለመሆኑን ወንጀሉ ሊመደብ የሚገባው በዝቅተኛ ደረጃ መሆኑን በወ/ሕ/አ/108 ድንጋጌ መሠረት የጽኑ እሥራት ቅጣት የሚጣለው ወንጀሉ ከባድ ሲሆን እና በተለይ የአደገኛነት ጠባይ ባላቸው አጥፊዎች ላይ ሆኖ እያለ የጽኑ እስራት ቅጣት አማራጭ መሠረት ተደርጐ እንዲወሰድ ዐ/ሕግ ያቀረበው ሐሳብ ተቀባይነት ሊኖረው የማይገባ እና መሠረት ተደርጐ መያዝ የሚገባው የቀላል እስራት አማራጩ መሆኑን የቀረበበት ሪከርድ አለመኖሩ ባለትዳር እና የሶስት ህፃናት ልጆቹን ጨምሮ የቤተሰብ አስተዳዳሪ መሆኑ በኤርትራ መንግስት የተቃጣውን ወረራ ለመመካት በውትድርና ገብቶ ማገልገሉ እና በጦርነቱ ምክንያት ቋሚ የአካል ጉዳት የደረሰበት መሆኑ ራሳቸውን ችለው በአራት የማቅለያ ምክንያትነት ሊያዙለት የሚገባ መሆኑን በዝርዝር በመግለጽ እና በቅጣት አስተያየቱ የተካተቱ ፍሬ ነገሮችን የሚያረጋግጡ ማስረጃዎችን በማያያዝ ፍ/ቤቱ እስካሁን የታሰረበትን የአንድ ዓመት ከሁለት ወር ከ25 ቀን በቂ አድርጐ እንዲያሰናብተው ይህ ታልፎ ተጨማሪ ቅጣት የሚወሰንበት ከሆነ ቀሪው የቅጣት መጠን ከመፈፀም ታግዶ እንዲቆይ ትዕዛዝ እንዲሰጥለት እና በተሽከርካሪው እና በቤቱ ላይ የውርስ ትዕዛዝ እንዲሰጥለት ዐ/ሕግ ያቀረበው ጥያቄ ተቀባይነት የለውም እንዲባልለት የጠየቀ ሲሆን ፍ/ቤቱም ጉዳዩን መርምሮአል፡፡

በዚህ መሠረት በድንጋጌው ስር ከተቀመጡት ሶስቱ የቅጣት አማራጮች መካከል በተከሳሹ ላይ ለሚጣለው ቅጣት ሶስተኛው ማለትም የጽኑ እስራት የመቀጮ አማራጭ መሠረት ተደርጐ እንዲያዝ ዐ/ሕግ ያቀረበውን ሃሳብ ፍ/ቤቱ ተቀብሎአል በሌላ በኩል ድንጋጌው ሶስተኛውን የቅጣት አማራጭ የደነገገው የወንጀሉን የአፈፃፀም ከባድነት በመስፈርትነት በመውሰድ መሆኑን ከድንጋጌው አነጋገር መገንዘብ የሚቻል በመሆኑ በክብደቱና በአፈፃፀሙ ወንጀው ሊመደብ የሚገባው ዐ/ሕግ እንደጠየቀው በከባድ ሳይሆን በመካከለኛ ደረጃ መሆኑን ፍ/ቤቱ ተገንዝቦአል በመካከለኛ ደረጃ ለተመደበ ወንጀል በመመሪያው የተቀመጠው ፍቅድ ስልጣን ከሁለት ዓመት እስከ ሶስት ዓመት የሚደርስ ሲሆን ከዚህ ፍቅድ ስልጣን ውስጥ በተከሳሹ ላይ መነሻ ተደርጐ መጣል የሚገባው የሁለት ዓመት ከሁለት ወር ጽኑ እስራት እና የብር አንድ ሺህ መቀጮ እንዲሆን ፍ/ቤቱ ወስኖአል፡፡ ይህ የእስራት ቅጣት መጠንም በአባሪ አንድ በእርከን 11 ሥር የሚወድቅ ነው መነሻ ተደርጐ የተያዘ የቅጣት መጠን በማክበጃ እና /ወይም በማቅለያ ምክንያቶች ከፍ ወይም ዝቅ ሊደረግ የሚችል ሲሆን በዐ/ሕግ በኩል የቀረበም ሆነ በፍ/ቤቱ የተገኘ የማክበጃ ምክንያቶች የለም ተከሣሹ የመልካም ፀባይ ባለቤት የነበረ መሆኑ በመደበኛ የማቅለያ ምክንያትነት ሊያዝለት የሚገባ ሲሆን በማስረጃ በተረጋገጠው ተከሣሹ በሀገራችን ላይ በኤርትራ መንግስት የተቃጣውን ወረራ ለመመከት የውትድርና አገልግሎት መስጠቱ እና በውትድርና አገልግሎቱም ቋሚ የአካል ጉዳት የደረሰበት መሆኑ

በወ/ሕ/አ/86 መሠረት በአንድ ልዩ የማቅለያ ምክንያትነት ሊያዝ የሚገባ መሆኑን ፍ/ቤቱ ተገንዝቦአል ከላይ የተጠቀሱት ሁለት የማቅለያ ምክንያቶች የፍቅድ ስልጣኑን መጠን ከእርከን 11 ወደ እርከን 7 ዝቅ የሚያደርጉት ሲሆን የመቀጮው መጠንም በተመሳሳይ ስሌት ዝቅ መደረግ ይኖርበታል፡፡ በመሆኑም ከላይ የሰፈረውን ዝርዝር በማጠቃለል ተከሣሹ ከዚህ ጉዳይ የታሰረው የሚታሰብለት በአንድ ዓመት ከአንድ ወር ጽኑ እስራት እና በብር አምስት መቶ መቀጮ እንዲቀጣ ፍ/ቤቱ በወ/ሕ/ሥ/ሥ/ቁ 149 (5) መሠረት ወስኗል፡፡

**<u>ትዕዛዝ</u>**

1. በፀረ ሙስና ልዩ የሥነ ሥርዓት የማስረጃ ሕግ አዋጅ ቁጥር 434/97 በአንቀፅ 30(1) እና (2) በተመለከተው መሠረት የውርስ አቤቱታውን ከስድስት ወራት በኋላ እንዲያቀርብ ትዕዛዝ ተሰጥቶአል፡፡
2. ተከሣሹ የተወሰነበትን የአንድ ዓመት ከአንድ ወር ጽኑ እስራት ቅጣቱን ማጠናቀቁን ከመዝገቡ ማረጋገጥ ስለተቻለ መቀጮውን ገቢ ማድረጉ ሲረጋገጥ የሚፈለግበት ሌላ ጉዳይ አለመኖሩን አረጋግጦ እንዲቀለው ለማ/ቤት ይፃፍ፡፡
3. በጥፋተኛነቱም ሆነ በቅጣት ውሳኔው ቅር የተሰኘ ወገን ይግባኝ የማለት መብት እንዳለው በችሎት ተነግሯል፡፡
4. እልባት ያገኘ ስለሆነ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡